# የአርቲስት ፀጋዬ ስሜ ባህላዊ ዘፈኖች ይዘት ትንተና

በ

በሜሮን ውንዳ

የአርት ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟሟላት የቀረበ ጥናት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# የአርቲስት ፀጋዬ ስሜ ባህላዊ ዘፈኖች ይዘት ትንተና

**በ**

**በሜሮን ውንዳ**

የአርት ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ
ነጥቦች ከፊሉን ለማሞሟላት የቀረበ ጥናት

አማካሪ
ገዛኸኝ ጌታቸው /አቶ/


የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ


ሰኔ 2002 ዓ.ም

# ምስጋና

- በእመብርሃን እርዳታ በቅዱስ ኡራኤል ምልጃ ሁሉን እንድችል ያደረከኝ አምላክ ምስጋናዬን ተቀበለኝ፡፡
- አባቢ እና ማሚ ለኔ እዚህ መድረስ እና ለጥናታዊ ጽሑፌ መሳካት ላደረገላችሁት ትልቅ አስተዋፅኦ እና እገዛ በጣም አመሰግናለሁ፡፡
- አማካሪዬን አቶ ገዛኸኝ ጌታቸው ከልብ አመሰግናለሁ፡፡
- የተለያዩ ሀሳቦችን በመስጠት ለተባበረኝ ለአርቲስት ፀጋዬ ስሜ እና የአርቲስቱን ስራዎች በመሰብሰብ ለተባበረኝ ለፍሉት ሙዚቃ ቤት ባለቤት ለአቶ ጉልላት ሀብቴ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡
- ደጄ፣ ሴፋሽ፣ እዮ፣ ቶም፣ ሮዬ፣ ማሂ፣ መቅዲ፣ ሳይመን፣ ቡርቴ እና ናቲ ሁላችሁንም ገለቶማ፡፡
- የኔን ስኬት ለማየት ጓግተሽ የተለያዩ ሀሳቦችን በመስጠት ከጎኔ ላልተለየሽኝ አክስቴ ንጋት እና ቤተሰቦችሽ ማለት የምችለው አመሰግናለሁ ብቻ ነው፡፡
- የተለያዩ ሃሳቦችን በመስጠት ከጎኔ ላልተለያችሁኝ ጓደኞቼ እሙዬ፣ ካልሽ፣ ዘኪ፣ ሳርች እና ስማችሁን ያልጠቀስኳችሁ ጋደኞቼ በሙሉ አመሰግናለሁ፡፡
- በመተየብ ለተባበረችኝ ነፂ አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

ምስጋና

## ምዕራፍ አንድ ........................................1

1. መግቢያ ........................................1
   - 1.1. ዳራዊ ምልከታ ........................................2
   - 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................3
   - 1.3. የጥናቱ አላማ ........................................4
   - 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................4
   - 1.5. የጥናቱ ገደብ ........................................4
   - 1.6. የጥናቱ ዘዴ ........................................5

## ምዕራፍ ሁለት ........................................6

2. ንድፈ ሐሳባዊ ምልከታና የተዛማጅ ጥናት ቅኝት ........................6
   - 2.1. የባሕላዊ ዘፈን ምንነት ........................................6
   - 2.2. የዘፈን ግጥም ምንነት........................................9
   - 2.3. የዘፈን ግጥም ባሕሪያት ........................................10
   - 2.4. የዘፈን ግጥም አይነቶች ........................................12
   - 2.5. የተዛማጅ ጥናት ቅኝት ........................................13

## ምዕራፍ ሦስት -------------------------------------------17

3. የአርቲስት ፀጋዬ ስሜ ባህላዊ ዘፈኖች ይዘት ትንተና ..................17
   - 3.1. ጋብቻን በተመለከተ የተዜሙ ........................................17
     - 3.1.1. ያሁዪባሶ ........................................17
     - 3.1.2. እንሾሽላ ........................................20
     - 3.1.3. ዬዎሬ ........................................22
     - 3.1.4. ልሙ ........................................25
   - 3.2. ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮችን በተመለከተ የተዜሙ ....................27
     - 3.2.1. ወሴ ባሳ ........................................27

3.2.2. ኬር ዬኧ፧ን ……………………………………………………30
3.2.3. የሻልቢ …………………………………………………...32
3.2.4. ለፊ ……………………………………………………………34
3.2.5. ኧዲሽ ባላገር ነው ……………………………………..35
3.2.6. ምኔቦ …………………………………………………...38

**ምዕራፍ አራት……………………………………..40**

ማጠቃለያ…………………………………………………………40
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው
ዋቢ ጽሑፎች
አባሪ

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ሙዚቃ ከማዝናናቱ ባሻገር የሰውን ልጅ መንፈስ የማረጋጋት ኃይል እንዳለው ይነገርለታል:: ሰዎች ሙዚቃን ሀዘናቸውንና ደስታቸውን ይገልፁበታል:: የወዱድትን ያሞግሱበታል የጠሉትን ይነቅፉበታል ለመግባቢያነት ለስራ ማበርታቻነት....... ወዘተ ሀሳባቸውን ለመግለፅ እንደ ዋነኛ መሣሪያቸው ይጠቀሙበታል:: ሀሳባቸውን በሚገልፁበት ወቅት እንደ ብሔረሰቡ ዜማ ምት እና እንቅስቃሴ ይታጀባል ከላይ የተጠቀሱት መልእክቶች እና ሌሎችም የሚተላለፉት በሙዚቀኛው አሊያም በዜማ አውራጁ አማካኝነት ነው::

በአሁኑ ወቅት የሀገራችንን ሙዚቃ ባህላዊ እና ዘመናዊ በማለት መክፈል ይቻላል ባህላዊ ተብለው ከሚጠቀሱት ዜማዎች ውስጥ የሠርግ፣ የአዝማሪ ዘፈን፣ ቀረርቶ፣ የልጆች ጨዋታ እና የእረኛ ዜማ በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዘመናዊ ተብለው የሚመደቡት የውጪው አለም የሚዚቃ ተፅዕኖ ጎልቶ የሚታይባቸውና ከባህላዊ የሚዚቃ ስልት ውጭ ያሉትን ያጠቃልላል::

ይህ ጥናታዊ ጹሑፍ ባህላዊ ዘፋኝ በሆነው ‹‹አርቲስት ፀጋዬ ሰሜ ባህላዊ ዘፈኖች ይዘትትንና ››ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጹሁፍ ውስጥ አርቲስቱ የብሔረሰቡን ማንነት ባህል እና ስርዓቱን የሚገልፁበትን ባህላዊ ዘፈኖች ይዳሰሳል፡፡ እነዚህ ባህላዊ ዘፈኖች በአሁኑ ወቅት ብሔረሰብ እየተዋቸውና እየረሳቸው የመጡትን ስነቃሎች አካተው የያዙ ናቸው::

ይህን ጥንታዊ ጹሑፍ ለማዘጋጀት ስለ ዘፈን ግጥም የተፃፈ መጽሐፍትን በመመልከት አንዳንድ ነጥቦች እወስዳለሁ፡፡ ከርዕሱ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ተዛማጅ ጥናት ፁሁፎችን እንደ መነሻነት እጠቀማለሁ፡፡ ይህ ጥንታዊ ጹሑፍ የሚያተኩረው በክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ ባህላዊ ዘፈኖች ላይ እንደመሆኑ መጠን ከተዛማጅ ጹሑፎች በተጨማሪ ስለ ብሔረሰብ ባህል ጠንቅቀው ከማያውቁ ሰዎች አንዳንድ መረጃዎች እሰበስባለሁ፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በብሔረሰብ መሀል በማድጌ በምልከታ ያዳበርኳቸውን ልምዶች ለጹሑፍ እንደ መንደርደሪያነት እጠቀምባቸዋለው፡፡ በአርቲስቱ ሥራዎች ውስጥ የሚገኙትን ለጥናቱ የመረጥኳቸውን ጠንከር ያሉ ባህላዊ ይዘት አላቸው ያልኳቸውን ዘፈኖች ከሚያነሱት ርዕስ ጉዳዬች አንፃር በመከፋፈል ይዘታቸውን ለመተንተንና ለማብራራት ጥረት ተደርጓል፡፡

# 1.1 ዳራዊ ምልከታ

ይህ "የአርቲስት ፀጋዬ ሰሜ ባህላዊ ዘፈኖች ይዘት ትንተና" የተሰኘው ርዕስ የሚያተኩረው በክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ ባህላዊ ሙዚቃዎች ላይ ሲሆን የባላገሩ ሕዝብ ባህሉን፣ ወግና ልማዱን፣ የህይወት ፍልስፍናውን፣ እምነቱን፣ የአኗኗር ዘይቤውን….. ወዘተ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፈው በስነ ቃል በዜማ እንዲሁም በክዋኔ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብም የተለያዩ ባህላዊ እሴቶቹን ለትውልድ ከሚያስተላልፍባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው ባህላዊ ዜማዎቹ ናቸው:: የክስታኔ ጉራጌ ብሄረሰብ የሚገኘው፡-

> "በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች መስተዳደር በጉራጌ ዞን ሶዶ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በሰሜን ከብቶች ሜጫ ኦሮሞ፣ በደቡብና ምዕራብ ከመስቃን ደቢ. ወለኔና ገደባኖ በምስራቅ ከአርሲ ኦሮሞ ጋር ይዋሰናል የክስታኔ ጉራጌ ክልል በአሁኑ ጊዜ በ21 የቦታ ስሞች የተከፈለ ሲሆን እነዚህም ዋጮ፣ ኑርና፣ አማውቴ፣ ገሬኖ፣ ሜልኮ፣ ገሜሴ፣ አይገዳ፣ ዘመቴ፣ ጎተጌ፣ እንደርዥጋን፣ አንገተጌ፣ ዳሙገነት፣ ገንዝ፣ አይመለል ፣መሠረተ ወገራም፣ እንደበዬ፣ አደሌ፣ ቀሽትና አምባሬ እንዲሁም ዱግዳና አራት ናቸው" (ድንበሩ እና ሌሎች 19 87 20) በማለት የቦታ ክፍፍሎች አስቀምጠዋል በነዚህ በ21 የቦታ ክፍፍሎች ውስጭ 54 ቀበሌ ገበሬ ማህበራት ይገኛሉ::

የክስታኔ ብሔረብ ዋናው መተዳደሪያው ግብርና ሲሆን ከብት እርባታና አልፎ አልፎ የንብ እርባታዎችን በመተዳደሪያነት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ የክስታኔ ብሔረሰብ አብዛኛውን የግብርና ሂደቶች የሚያከናውነው የተፈጥሮ ዝናብ ወቅትን በመጠቀም ኃላቀር የሆነ የአስተራረስ ዘዴን በመጠቀም ነው::

የክስታኔ ጉራጌ አካባቢ የአየር ጠባይ ደጋ ውይና ደጋና ቆላ ሲሆን በነዚህ አካባቢዎች የተለያዩ የአትክልትና የፍራፍሬ አይነቶች ይመረታሉ የጉራጌ ሕዝብ በተለየ የሚታወቅበት የተለየ የተክል አይነት እንሰት በመባል ይታወቃል ይህ የተክል ዐይነት ድርቅን ለረዥም ጊዜ የመቋቋም አቅም እንዳለው ይነገርለታል፡፡ ብሔረሰቡ ከዚህ የተክል ዐይነት የተለያዩ ምግቦችን በማዘጋጀት ይጠቀማል::

ክስታኔ ብሔረሰብ የራሴ የሚላቸው የሰርግ የለቅሶ የውግዘት የመሃላ የስራ…. ወዘተ የመሳሰሉ ሰርዓቶች አሉት፡፡ እነዚህን ስርዓቶች በዜማና በሥነ-ቃሎች አማካኝነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፏቸዋል::

ይህ ጥናታዊ ጹሑፍ የሚያተኩረው የክስታኔ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆነውና የብሔረሰቡን ሙዚቃ በመጫወት ከሚታወቁ አርቲስቶች መሃከል አንዱ በሆነው አርቲስት ፀጋዬ ስሜ (ወሴባሳ) ሥራዎች ውስጥ የብሄረሰብ ባህላዊ እሴቶች እንዴት እንደሚገልፁ ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ የተደረገውን ጥረት ማመላከት ይሆናል::

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ሙዚቃን ከማስማት ባሻገር ስለምን እንደሚናገር የማድመጥና የመረዳት ችሎታ ባልነበረኝ ወቅት እንኳን ለጥናቴ የመረጥኩት የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ ሙዚቃ ዜማና ምት ተጣምረው የሚፈጠሩት የተለየ ስሜት ውስጤን ያስደሰተኝና ያዝናናኝ ነበር፡፡ ካደኩኝ በዋላም ከዘመናዊ ሙዚቃ ይበልጥ ልጅ ሁኜ የተለየ ስሜት በመፍጠር ያዝናናኝ የነበረውን ባህላዊ ሙዚቃ ትኩረት ሰጥቼ ማድመጥ ጀመርኩ::

እኔ የተገኘሁበት ቤተሰብ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሲሆኑ ያደኩበት አካባቢ ከሚኖሩት ነዋሪዎች አብዛኛውን ቁጥር የሚይዘው የጉራጌ ብሄረሰብ ተወላጆች ናቸው፡፡ ወላጆቼ ስለ ብሔረሰብ ባህል ስርዓትና ቋንቋውን እንዳውቅ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገውልኛል፡፡ባደኩበት አካባቢ የሚኖሩ የብሄረሰብ ተወላጆች ቋንቋውን ለመግባቢያነት ስለሚጠቀሙበትና የተለያዩ ባህሎችን ሲያከብሩ የሚያዜሟቸውን የብሔረሰብ ዘፈኖች አዘውትሬ በመስማቴ ለብሄረሰብ ሙዚቃ የተለየ አክብሮት እና ፍቅር ስላደረብኝ የድግሪ ማሚያ ጹሑፌን የብሔረሰቡን ሙዚቃ በሚጫወት አንድ አርቲስት ስራ ላይ አደረስኩ፡፡

- የቋንቋው ተናጋሪዎች እና የብሔረሰቡ ተወላጆች ዘፈኑን ሰምተው ከመዝናናት ባሻገር ሊተላለፍ የፈለገው መልዕክት ምንድን ነው የሚለውን አጥኚዋ ለመተንተን ሙከራ በምታደርግባቸው ዘፈኖች በማሳየት ከዕለት ተዕለት ንሮዋቸው ጋር በማዛመድ እንዲመለከቱት ለማድረግ ጥናቱ እንዲካሄድ ምክንያት ሆኖዋል::

➢ ቀደም ስል የብሔረሰቡን ባህላዊ ዘፈን በሚያዜም አርቲስት ዙሪያ የተደረገ ምንም ጥናት ባለመኖሩ::

## 1.3 የጥናቱ አላማ

1. የብሄረሰብ ተወላጅ ለሆኑት የአገራቸውን እና ያደጉበትን ባህል ጠንቅቀው እንዲያውቁት እና እንዲያስታውሱ ማድረግ፡፡
2. ዘፈኖቹ የብሔረሰቡን ባህሎች እንዳይረሱና የተረሱትን እንዲታወሱ ያደረጉትን አስተዋፅኦ ማሳወቅ፡፡
3. የብሔረሰብ ተወላጅ ላልሆነው ሕብረተሰብ ስለጉራጌ ብሔረሰብ ባህል አንዳች ነገር ማሳወቅ፡፡
4. በግጥሞቹ ውስጥ የብሔረሰብን ማንነት ማሳወቅ ማሳየት፡፡
5. የብሔረሰብን ባህላዊ ሙዚቃ በተመለከተ የሚሰጠውን ትንተና ለተተኪው ትውልድ በጽሑፍ ሰነድ ማቆየት::

## 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

➢ የዚህ ጥናት አስፈላጊነት አርቲስት ፀጋዬ ስሜ ባወጣቸው 4 ካሴቶች ውስጥ በሚያነሳቸው ርዕስ ጉዳዮች ስር የሚገኙትን ቁሳቁሶች አልባሳት እና የተለያዩ የብሔር ሰብን ማንነት የሚገልፁ ጉዳዮችን ነማካተቱ ለወደፊት የብሔረሰቡን ባህል በደንብ ዘልቆ ማወቅ ለሚፈልግ አጥኚ የአርቲስቱ ስራዎች ጠቋሚ የሆኑ መረጃዎችን መስጠት ነው፡፡

➢ የተረሱትን የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ ስነቃሎች አርቲስቱ እንዴት የቀደመ ትርጓሜያቸውን ሳይለቁ እንዳቀረባቸው ለአንባቢው በማሳወቅ ሌሎችም የብሔረሰቡ ስነ.ቃሎች በስፋት እንዲጠኑ የዚህ ጥናት መካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡

➢ በማንኛውም የግጥም ትንተና ላይ ለሚደረግ ጥናት እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ገደብ

ይህ «የአርቲስት ፀጋዬ ስሜ ባህላዊ ዘፈኖች ይዘት ትንተና የሚለው ጥንታዊ ጹሑፍ አርቲስቱ ባወጣቸው አራት ካሴቶች ውስጥ የሚገኙትን የባህላዊ ዘፈኖች ግጥሞ ይዘት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በአርቲስቱ ስራዎች ውስጥ 10 የሚሆኑት ዘፈኖች በ7

ቤት ጉራጌና ዶቢ እየተባለ በሚጠራው ጉራጌ ብሔረሰብ ቋንቋ የተዜሙ ሲሆኑ አጥኚዋ እነዚህን ዘፈኖች በጥናቷ ውስጥ አታካትትም::

ምክንያቱም

1. እንዚህ ዘፈኖች ተርጉሞ ለመተንተን የብሔረሰቡን ባህል ጠልቆ ማወቅ ያስፈልጋል። ስለሆነም አሁን በሚደረገው የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብና ከላይ የተጠቅሱት ሁለቱ የጉራጌ ብሔሮች መካከል ልዩነቶች በመኖራቸው ምክንያት ዘፈኖቹ በጥናቱ ውስጥ አይካተቱም::
2. ጥናታዊ ጹሑፉን አጠናቆ ለመስጠት ካለው የጊዜ እጥረት እና የገንዘብ አቅም አኳያ ቀደም ብለው የተጠቀሱት ብሔረሰቦች ዘፈኖች አይካተቱም::

## 1.6 የጥናቱ ዘዴ

አርቲስት ፀጋዬ ስሜ ባወጣቸው 4 የዘፈን ካሴቶች ውስጥ በሚገኙ ግጥሞች ላይ በመመርኮዝ ይዘታቸውን ይበልጥ ያተኮረበትን ጉዳይ በመመልከት እንደሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ በመከፋፈል ይዘታቸው ተተንትኗል። ይህን ለማድረግ የዘፈን ግጥሞቹን በጹሑፍ በመገልበጥ ደጋግሞ በማንበብ እና ግጥሙን ከዜማው ጋር አርቲስቱ ሲያዜመው በማድመጥና ተዛመጅነት ካላቸው ሥራዎች ጋር በማስተያየት ጥናታዊ ፁሁፉን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል።

ይህን ለማድረግ አጥኚዋ የተጠቀመችበት የምርምር ዘዴ የይዘት ትንተናን ሲሆን ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ይረዳሉ ተብሎ የታመነባቸው አስር ዘፈኖች በናሙናነት ተመርጠዋል። የመረጃ አሰባሰቡን በተመለከተ በዋናነት እንደመረጃ ግብዓት አጥኚዋ ለቋንቋውና ለባህሉ ያላትን እውቀትና ቅርበት ትጠቀማለች። በተጨማሪም እንደየአስፈላጊነቱ ከተለያዩ የብሔረሰቡ ተወላጆች አስፈላጊ መረጃዎች በማካተት ጥናቱ ተካሂዷል::

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ንድፈ ሀሳባዊ ምልከታና የተዛማጅ ጥናት ቅኝት

### 2.1 የባህላዊ ዘፈን ምንነት

የሰው ልጅ በራሱና በተፈጥሮ መካከል የሚከሰተውን ችግሮች ለመፍታት የሚያደርጋቸውን ትግሎቹን፣ መፍትሄዎቹን፣ ስልጣኔውን፣ የራሱን ማንነት፣ እምነቱን፣ አመለካከቱን፣ ባህሉን፣ የአኗኗር ዘይቤውን፣ ሀዘንና ደስታውን ባለው የስነ ቃል ሃብት በመጠቀም በግጥም በስድንባብ እና በማንጎራጎር ለትውልድ ሲያስተላልፍ ኖሯል። ሥነቃል መጠነሰፊ አገልግሎት የሚሰጥ የባህል መገለጫ መሆኑ ይታመናል። ስለሆነም እያንዳንዱ ማህበረሰብ ቁሳዊ ባህሉን፣ ወጉን እና ቋንቋውን ሳይቀር የሚያሳውቅበትና የሚያስተላልፍበት አንዱ መንገድ ስነቃል ውስጥ በሚካተተው ባህላዊ ዘፈን አማካኝነት ነው።

ሥነቃል የሰው ልጅ በእለት ተእለት የኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ክስተቶች የሚገልፀፅበት ሀብቱ ነው። ሥነቃል እንደ ስዕልና ቅርፃ ቅርፅ ካሉ የሰው ልጅ የሀሳብ መግለጫ መንገዶች የሚለይበት የራሱ የሆነ ባህሪ አለው። ይኸውም በቃል መግለፅና በድርጊት መታጀቡ ነው። ከትውልድ ወደ ትውልድ በቀላሉ በቃል የመተላለፍ ሀይልም አለው። ስነቃል በቃል መተላለፍ መቻሉ ብቻ ሳይሆን መከወን በመቻሉ ስሜትን የመከርከርና የመግዛት ሃይል ያለው ጥበብ ነው። የሰው ልጅ የስነቃል ስሜት የመግዛት ኃይል በመጠቀም ተፈጥሮአዊ ጥያቄዎቹን ይመለስበታል፣ ያጠፋውን ይገሰፅበታል፣ የወደደውን ያሞግሱበታል ያስተምርበታል ይህንንም የሚያደርገው የተለያዩ ቅርጾችን በመጠቀም ነው። ይህንን ሀሳብ ዘሪሁን አስፋው ሲገልፅ፡

> "የስነቃል አይነቶች ብዙ ናቸው። በየአገሩና በየባህሉ የተለያዩ የስነቃል አይነቶች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ በሁለት አባይት ቅርፆች ይካተታሉ። የመጀመሪያዎቹ በዘርውና በትረካ የሚነገሩ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ በግጥም ቅርጽ የሚቀርቡና የሚዜሙ ናቸው። በዝርው ከሚቀርቡት መሀል ተረት፣ አፈታሪክ፣ ሀተታ ተፈጥሮ፣ ምሳሌያዊአነጋገር፣ እንቆቅልሽ፣ ቀልድ ሌሎችም

ይገኙበታል፡፡ ከሚዜሙት ደግሞ ባህላዊ ዘፈኖችንና ዝማሬዎችን ሙሽን ፉከራንና ቀረርቶን መጥቀስ ይቻላል”፡፡

(ዘሪሁን፣ 1998፣ 28)

ከላይ እንደተገለፀው ባህላዊ ዘፈኖች ዜማ ለበስ ከሆኑት የስነ ቃል ዘርፎች የሚመደቡ ናቸው፡፡ እነዚህም ስለ ጀግንነት ስለ ክህደት ስለ ጥላቻና ስለ ፍቅር ይዜማሉ፡፡ ጋብቻ፣ ውግዘት፣ ምርቃት፣ ሥራ የሚዜሙባቸው አጋጣሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ዘፈኖች የሚዜሙት ዘመናዊነት እና ቴክኖሎጂ ባልተስፋፋበት የገጠሩ አካባቢ ነው፡፡

ወግና ልማድ፣ ታሪክ በመዜም ከሚተላለፉባቸው መንገዶች አንዱ ባህላዊ ዘፈን ነው፡፡ ይህ ባህላዊ ዘፈን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው በቃል በመነገር፣ በመዜምና በክዋኔ አማካኝነት ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ የስነ ቃል መገለጫዎች ናቸው፡፡ ባህላዊ ዘፈንም ከስነ ቃል ዘርፎች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ምክንያት ባህርያቱ ጐልተው ይታዩበታል፡፡

ከስነቃል ሁለት ዐበይት ቅርፆች መካከል ባህላዊ ዘፈን በአንዱ ውስጥ ተካቷል፡፡ ይህ በመሆኑም የስነ ቃል ባህርያት ተብለው የሚጠቀሱት ባህርያት ማለትም የአመንጪው ማንነት አለመታወቅ፣ ቡድናዊነት እና በክዋኔ መታጀብ በባህላዊ ዘፈኖች ላይ ከሌሎች የስነ ቃል ዘርፎች በይበልጥ ሰፋ ባለ መልኩ ይንፀባረቅባቸዋል፡፡ ዘሪሁን አሰፋው ስለ ባህላዊ ዘፈን ሲገለፁ፡-

> “በግጥም ከሚቀረቡትና ከሚዜሙት የስነ ቃል አይነቶች አንደኛው ወገን ባህላዊ ዘፈኖችን ያጠቃልላል፡፡ ባህላዊ ዘፈኖች በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ የሚዘፈኑ የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ መልኮች ሊያሳዩ የሚችሉ አስደሳች የስሜት መግለጫዎች ናችው፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ እንደየ ባህሉና እንደ አኗኗር ስልቱ ዘፈኖችና እንጉርጉሮዎች አሉት፡፡በእነዚህ ዘፈኖችና እንጉርጉሮዎች የማህበረሰቡ አባላት ደስታቸውንና ብሶታቸውን ፣ ምኞትና ፍላጐታቸውን ይገልጹባቸዋል፡፡ የባህላዊ ዘፈኖች አይነታቸው ብዙ ነው፡፡ የስራ ዘፈን፣ የክብረ ባህል ዘፈን፣ የሠርግ ዘፈን፣ የፍቅር ዘፈን፣ የአምልኮ ሥነ-ሥርአት ዘፈን፣ የልጆች ጨዋታ ዘፈን ወዘተ. . እየተባሉ ይመደባሉ፡፡” (ዘሪሁን፣ 1998፣ 46) በማለት አስፍረዋል፡፡

ባህላዊ ዘፈኖች እንደየብሔረሰቡ የአኗኗር ስልትና ባህል የሚለያይ ሲሆን እነዚህ ልዩነቶች እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራሴ የሚላቸው ባህላዊ ዘፈኖች እንዲኖሩት ትልቅ አስተዋፀኦ ያደርጋሉ ። የባህሉ ባለቤት የሆነው ህብረተሰብ ዜማውን በራሱ እንቅስቃሴና ምት በማጀብ ከመዜም በተጨማሪ ለባህላዊ ዘፈኑ የተለየ ገፀታን ያላብሱታል።

የዚህ ጥናታዊ ጹሑፍ አላማ ስለ ሰነ ቃል ምንነት ማሳወቅ አይደለም። ነገር ግን ጥናቱ የሚካሄደው በአንድ ብሄረሰብ ባህላዊ ዘፈን ግጥም ይዘት ትንተና ላይ በመሆኑ ባህላዊ ዘፈን የሚመደበው ከየት ነው ለሚለው የአንባቢ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ያህል የተፃፈ ነው።

## 2.2 የዘፈን ግጥም ምንነት

ዘፈን እንደ ሌሎች የኪነ ጥበብ ዘርፎች ሁሉ የሰው ልጅ ውስጣዊ ስሜት መግለጫ መንገድ ነው፡፡ በዘፈን ማንኛውም ሰው ፍቅሩን ፣ ጥላቻውን ፣ ደስታውን ፣ ሀዘኑን - - - ወዘተ ይገልፅበታል፡፡ ይህም የኪነ ጥበብ ዘርፍ በማንኛውም ኅብረተሰብ ባህል ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ በጥቅሉ በዘፈን ጥበብ ውስጥ የአንድ ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ የህይወት ገፅታ ሊንፀባረቅ ይችላል፡፡

ለአንድ ዘፈን አስፈላጊ ከምንላቸው ነገሮችመካከል ግጥም ፣ ዜማ ፣ ምት ፣ የዘፋኙ ድምፁ አወጣጥ እና ሌሎችም ለዘፈኑ የተዋጣ መሆን የራሳቸው አስተዋጾ ቢኖራቸውም የዘፈን ግጥም ግን ለዘፈኑ ህልውና ላቅ ያለ ቦታ ይዞ እናገኘዋለን፡፡

የዘፈን ግጥምን (ሌሪክ) በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ከነዚህም መካከል ሩዝ ሚለር እና ሮበርት Poetry An Introduction በተባለው መጸሐፋቸው ውስጥ

> "ሌሪክ የሚለው ቃል ሌየር (lyra) ከሚለው የሙዚቃ መሳሪያ የተወሰደ ሲሆን ግጥም ከሙዚቃ ጋር የምናገናኝበት፣ ቁጥብ የሆነ የሙዚቃ አንድ አካል ለሰሜት ቅርበት ያለው እንዲሁም በሙዚቀኞች ወይም በገጣሚያን የሚሰራ ነው" (Ruth miller and Robert , 1981; – 175 ) በማለት ስለ ሌሪክ ፅፈዋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው መፅሐፍ በተጨማሪ

> "ሌሪክ ሌሪኮስ (LYrikos) ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ጥንት በሌሪ ባለሰባት ሴሪ ክራር መሰል የሙዘቃ መሰሪያ የሚታጀብ የግድ ባይሆንም በምጣኔና በምታቸው ሙዚቃዊ ቃናን የሚፈጥሩ ግጥሞችን ሁሉ ያጠቃልላል"፡፡ በማለት Academic American Encyclopedia ገልፀዋል፡፡

ይሁን እንጂ ሌሪክ ግጥም ሁልጊዜ ለመዘፈን ብቻ የሚገጠም ግጥም ነው ማለት አይቻልም፡፡ ሌላው ስለ ሌሪክ ምንነት ብያኔ ከሰጡት መካከል ሲ ዲይ ሊዊስ ደግሞ "ሌሪክ ለሙዚቃ ተብሎ የሚገጠም ወይም የሚፃፍ ግጥም ነው"፡፡ (C. Darlewis 1965:- 17)

Academic American Encyclopedia የሰጠው ብያኔና ሲ. ዲ.ይ ሊዊስ የሰጠው ብያኔ የተለየ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ሌሪክ የግድ ለመዘፈን ብቻ ተብሎ የሚገጠም ግጥም እንዳልሆነ ሲጠቅስ ቀጥሎ ያለው ደግሞ ሌሪክ ለሙዚቃ ብቻ ተብሎ የሚፃፍ ግጥም መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ሌሪክ እራሱን የቻለ አንድ ወጥ ብያኔ እንደሌለው ነው፡፡

ከሀገር ውስጥ ፀሐፊያን መካከል የዘፈን ግጥምን (ሌሪክን) አስመልክቶ ስለ ምንነቱ ከገለፁት መካከል፡-

ያ ስሜት ኮርኩሮ
ያስገኛቸው ግጥሞች
ለደስታም ሆነ ወይም ለአንክሮ
አሉኝ በመዝገቤ አያሌ "ሌሪኮች"

(ገሞራው 19 66 51)

በማለት ሌረክን ስሜታዊ ግጥም እንደሆነ በራሱ በግጥም ብያኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ከስሜታዊነቱ ጋር በመያያዝ በሀገር ውስጥ ከታተሙት መጽሐፍት መካከል ስለ ሌረክ ብያኔ ብርሃኑ ገበየሁ፡-

> "ሌረክ ግጥም አጭር ሙዚቃዊ ከመዝሙርና ከእንጉርጉሮ የተያያዘ እጅጉን ስሜት ንክር ግጥም ነው፡፡ በሌላ አባባል ሌረክ የራሱን የገጣሚውን ገጠመኝ ስሜትና ህይወት ያንፀባርቃል"፡፡
>
> (ብርሃኑ 1996፣ 383) በማለት ስለ ሌሪክ ምንነት ይገልፃል::

ከዚህ በላይ በተለያዩ ምሁራን ስለ ሌረክ ምንነት የተሰጡትን ብያኔዎች ስንመለከት የተለያዩ ብያኔዎች በተለያዩ መንገድ እንደተሰጡ እንረዳለን፡፡ ስለዚህ የሌረክን ምንነት በተመለከተ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ መስጠት እንዳልተቻለ እና አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ እንዳልተገኘለት እንረዳለን::

## 2.3. የዘፈን ግጥም ባህሪያት

ሌሪካዊ ግጥም የተመረጠን የማኅበረሰቡን ገፅታ በማሳየት ረገድ እንደ ሌሎች የኪነ-ጥበብ ዘርፎች የሚጋራቸው ባህርያት ቢኖሩም ከሌሎች የሚለይበት ባህርያትም አሉት፡፡

ሌረካዊ ግጥም ሌሎች ግጥሞች ያላቸውን ባህርያት በሙሉ እንደያዘ አድርገን ማየት የለብንም፡፡ የሌረካዊ ግጥም ዋነኛ ባህሪውም የሰው ልጅ ውስጣዊ ጥልቅ ስሜት አውጥቶ ማሳየት መቻሉ ነው፡፡ ስለሆነም በሌረካዊ ግጥም የሰው ልጅ ፍላጎት፣ ምኞት፣ ሀዘን፣ ደስታ፣ ትዝታና ናፍቆት የመሳሰሉት ጥልቅ ስሜቶች ይገልፁበታል፡፡ ይህም በመሆኑ ለሚነሳው ርዕሰ ጉዳይ ገደብ የለበትም፡፡ ይህንን በተመለከተ "ሌሪክ እንደ አንድ የግጥም ቅርፅ እንፈርጀው እንጂ በልዩ ልዩ የዜማ ስልቶችና ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተፃፉ ግጥሞችን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ የአማረኛ ሌሪክ ግጥሞች ልዩ ልዩ ስልት ያላቸውን ባህላዊና ዘመናዊዉን ያካትታሉ"፡፡ (ብርሃኑ፣ 1996፣ 384) በማለት ለሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይ ገደብ እንደሌለበት እና ልባችን የሚሰማውን ወይም ደግሞ ራዕያችን የሚጠቁመንን ስሜት ሁሉ ይገልፅልናል::

የሀገራችን የዘፈን ግጥሞች ባህርያት በተመለከተ በቂ የሆነ በመረጃ የተደገፈ ጥናት አናገኝም፡፡ በአጠቃላይ ሌሪክ እንደ ማንኛውም ዐይነት የግጥም ፈለግ የተከተለ ቢሆንም ከሌሎች የግጥም አይነቶች የሚለይበት የራሱ የሆነ ባይርይ ያለው ነው፡፡

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የሚገኙ ሀያሲያን ሌሪክን ካሉት ዋና ዋና ባህርያት ማለትም ከሙዚቃዊው ባህሪው ውጭ ያሉትን አንፃራዊ ብያኔ ለመስጠት ሞክረዋል፡፡ ሰላማዊት ይልማ (ዲማፅ) Hegel Colerdge millr እና ሌሎችንም ምሁራን ጠቅሳ እንደፃፈችው ስለ ሌረክ በታሰበ ቁጥር እነዚህ ሀያሲያን በተደጋጋሚ ከሚጠቅሷቸው ባህርያት መሀል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ሌሪክ አጭር መሆን አለበት፡፡
2. ሌሪክ አንድ ወጥ መሆን አለበት፡፡ የግጥሙ ትንሽ ክፍል የቀረውን ሌላውን ክፍል እንዲደግፍና እንዲያብራራ ሆኖ እርስ በርሱ በተሳሰረ ሁኔታ በጥንቃቄ መደራጀት አለበት::
3. በሌሪክ የሚነሳው ሀሳብ ከጥልቅ ስሜት የመነጨና ድንገታዊ መሆን አለበት፡፡
4. ሌሪክ ግለሰባዊነት አጉልቶ የሚያሳይና ግላዊ አገላለፅ ያለው መሆን አለበት፡፡
5. ሌሪክ በአይምሯችን ውስጥ ተደብቆ ያለውን ስሜት ወይም ፍላጐት አውጥቶ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡
6. በሌሪክ የሚነገረው ነገር ተደማጭ መሆን አለበት፡፡ (ሰለማዊት 1991 ፣ 101)

ከላይ ከተጠቀሱት ባህሪያት በመነሳት ሌሪካዊ ግጥም በጥልቅ ግላዊ ስሜት ሊመጣና ሊገለፅ የሚችልን ጉዳይ ሁሉ ያነሳል። ከነዚህ በተጨማሪ ሌሪካዊ ግጥም አንድ ወጥ መሆን አለበት።

## 2.4. የዘፈን ግጥም ዐይነቶች

የዘውግ አከፋፈል እና ስያሜዎች ውስን ናቸው። ለምሳሌ በእንግሊዝ፣ በፈረንሳይ ወይም በጃፓን ባህል ያሉ የግጥም ዐይነቶች አከፋፈልና የግጥም አይነቶች ስያሜ የአማርኛ ግጥሞችን ለመከፋፈል እና ለመበየን አያገለግልም። ምክንያቱም የሥነ ግጥም ጥናትና ትንታኔ መሠረት የሚያደርጋቸው እሳቤዎችና መመዘኛዎች ከዚያው ከተጠኘው ባህል የፈለቁ በዚያው ሥራዎቹ ከበቀሉበት ማህበረ ባህላዊ አካባቢ የመነጨ መሆን ስላለባቸው ነው። (ብርሃኑ፣ 1996፣ 350)።

የዘፈን ግጥም ዐይነታቸውን በተመለከተ የተለያዩ ጸሐፊዎች እና ምሁራን በተለየ መልኩ ይከፍሏቸዋል። ይህ የሚያሳየው ደግሞ በስነ ግጥም ጥናት አንድ ወጥ የሆነ የዘፈን ግጥሞች ዐይነት እንደሌለው ነው። የልዩ ልዩ ባህሎች የዘፈን ግጥም ዐይነቶች አከፋፈል ልዩ ልዩ መስፈርቶችን መሰረት ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህም በዚህ ጥናት የዘፈን ግጥም ዐይነቶች በተለያዩ መፅሐፍት የተለያዩ ሆነው ስለተገኙ በአማርኛ (ሌሪክ) የዘፈን ግጥሞች ውስጥ የሚካተቱ ልዩ ልዩ ስልት ያላቸውን ግጥሞች መዳሰስ ተገቢ ነው ብላ አጥኚዋ ታምናለች። ከዚህ በመነሳት ብርሃኑ ገበየሁ በአማርኛ (ሌሪክ) የዘፈን ግጥሞች ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው ካላቸው ውስጥ መዲና፣ ሙሾ፣ የፍቅር፣ የትዝታና የናፍቆት ግጥሞች ዋና ዋናዎች እንደሆኑ ገልፀዋል።
ከላይ የተጠቀሱትንም በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**መዲና**

> "ከታወቁ ነገር የአማርኛ የዜማና የግጥም ስልቶች አንዱ ነው። መዲና እንደ አንድ የሌሪክ ግጥም አይነት በተለየ መንፈሳዊና አንክሮአዊ ለሆኑ፣ ማሰብና ማሰላሰል፣ ወደ ውስጥ ምልከታ የሚታይባቸውን ሐሳቦችና ስሜቶች የሚነገሩባቸውን ግጥሞች ሁሉ ያጠቃልላል።" (ብርሃኑ 1999፣ 384— 385)

**ሙሾ**

> "ሙሾ የሐዘን እንጉርጉሮ ነው። በነባሩ ቃል ግጥምም፣ በዘመናዊ ግጥሞችም ውስጥ ቢሆን ብዙ የአማርኛ ገጣሚያን ወዳጆቻቸው ወይም ለሚያደንቋቸው ሰውች ሞት የጻፏቸው የሐዘን እንጉርጉሮዎች በርካታ ናቸው። እነዚህ እንጉርጉሮዎች እንደ ሙሾ በአንድ በኩል የሟችን ታላቅነትና ሙያ የሚያዘክሩ፣ የሟችን ገድል የሚያጣቅሱ፣ በሌላ በኩል ገጣሚው በሰውየው ሞት ያደረበትን መሪር ሐዘን የሚገልጹ ናቸው"። (ብርሃኑ 1999፣ 385 — 386)

**የፍቅር፣ የትዝታና የናፍቆት ግጥሞች**

> "በሌሪክ ግጥም ከሚገለጹ ጥልቅ ሰብዓዊ ስሜቶች ጥቂቶች ፍቅር፣ ትዝታና ናፍቆት ናቸው። ሌሪክ እነዚህን ግላዊ ስሜቶች ለመግለጽ የሚያስችል አብይ የቋንቋ ጥበብ ነው። በአማርኛ የፍቅር፣ የትዝታና የናፍቆት ግጥሞች አያሌ ናቸው። የፍቅር ግጥሞች ትኩረታቸው የአፍቃሪውን ስሜት መግለጽ ይሁን እንጂ ሁልጊዜ ተፈቃሪን የሚያወድሱ ብቻ አይደሉም። ከፍቅር ጋር የተያያዙ ስሜቶች አያሌ ናቸው። ስለዚህም ገጣሚው የፍቅረኛውን ውበት አንስቶ ሊያወድስ፣ ደግነቷን ታላቅነቷን ጠቅሶ ሊያደንቅ ይቻለዋል፡፡ ቅሬታንና ወቀሳን፣ አለመርካትንና ቀየሜታን የሚዘረዝሩ የፍቅር ግጥሞችም ጥቂት አይደሉም እነዚህ መሰል ግጥሞች አንድም መልዕክታቸው፣ ሌላም ድምጸታቸውና የሚስሉት ድባብ በአንባቢ መንፈስ ታትሞ ይኖራል"። (ብርሃኑ 1999 ፣ 389)

## 2.5. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የዘፈን ግጥሞችን ርዕስ አድርገው በመምረጥ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ተሰርተዋል፡፡ ከነዚህ መካከል አበዛኛዎቹ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋ እና ባህል ላይ ተመስርተው የተሰሩ ናቸው። እነዚህ ጥናቶች በብዛት የሚያተኩሩት በአንድ ብሔረሰብ የለቅሶ፣ የሰርግ፣ የምርቃት፣ ሥርዓት …ወዘተ በመሳሰሉት ሥርዓቶች ላይ የሚዜው የዘፈን ግጥሞች መሠረት ያደረጉ ሲሆኑ እነዚህ በአንድ ባህል ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የተሰሩትን ጥናቶች ብመለከትም ለጥናቱ ይበልጥ ቅርበት አላቸው ብዬ ያመንኩባቸውና በአንድ ዘፋኝ ስራ ውስጥ አልያም

በተለያዩ አርቲስቶች ስራ ውስጥ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት የተዜሙ የዘፈን ግጥሞችን በመምረጥ ትንተና ያደረጉትን ጥናቶች በተዛማጅ ጽሑፍነት እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡

1. **አለማሁ ጌታቸው**

“አርቲስት አለማየሁ እሸቴና ስራዎቹ” በሚል ርዕስ 1993 ዓ.ም የቀረበ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ አርቲስት አለማየሁ እሸቴ ከልጅነት ጥናቱ እስከተካሄደበት ወቀት ያለውን የህይወት ታሪክ እና በ1950-60ዎቹ የተጫወታቸውን ዘፈኖች የሚተነትን ጥናታዊ ጽሑፍ ነው፡፡

የአለማየሁ ጌታቸው ጥናታዊ ጹሑፍ እና አሁን የሚካሄደው ጥናት የሚያመሳስላቸው ሁለቱም በአንድ አርቲስት የተለያዩ የዘፈን ግጥሞች ላይ ይዘት ትንተና ማድረጋቸው ሲሆን የሚለያዩት ደግሞ ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው የአርቲስቱ የህይወት ታሪክ ላይ ሳይሆን የአርቲስቱን የዘፈን ግጥሞች መተንተን ላይ ነው፡፡ የአለማየሁ ስራ ግን የአርቲስቱን አጠቃላይ የህይወት ታሪክ፣ ዉልደት፣ እድገት እና በስራ አለም ውስጥ የነበሩትን ሂደቶች የሚዳስስና የሚመለከት በመሆኑ ልዩነት አላቸው፡፡

2. **ሊሻን ተፈራ**

“የአስናቀች ወርቁ የፍቅር ዘፈኖች ግጥም ቅርጽና ይዘት ግምገማ” በሚል ርዕስ በ1974 ዓ.ም የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናታዊ ጹሑፍ ቅርፅና ይዘትን ማዕከል አድርጎ የተሰራ ሲሆን በቅርፅ ውስጥ የተለያዩ ጉዳዮችን በማንሳት ዳሳለች፡፡ ጥናታዊ ጹሑፉ የተካሄደባት አርቲስት ሴት በመሆኗ ስለተቃራኒ ፆታ ፍቅር የዘፈነቻቸው ዘፈኖች ላይ ትኩረት በመስጠት ትንተና የተደረገበትና አርቲስቷን በማነጋገር የህይወት ታሪኳን ያካተተ ጽሑፍ ነው፡፡

የሊሻን ጥናት ከአሁኑ ጋር የሚያመሳስለው በአንድ አርቲስት ስራዎች ውስጥ የሚገኙትን የዘፈን ግጥሞች ይዘት መተንተኑ ነው፡፡ የሚለየው የሊሻን ጥናት ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ዲማፅ አርቲስቷን ቃለ መጠይቅ በማድረግ የህይወት ታሪኳን

ያካተተና የፍቅር ዘፈኖችን ብቻ የሚመለከት መሆኑ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ከይዘት ትንተናው ጐን ለጐን ቅርፁን የሚመለከት መሆኑ ጥናታዊ ጽሑፋችንን እንዲለያይ ያደርገዋል፡፡

3 ሠላማዊት ይልማ

"ከ1987-1990 ዓ.ም በካሴት ታትመው በገበያ ላይ የዋሉ የአማረኛ የዘፈን ግጥሞች ቅርፅና ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ በ1991 ዓ.ም የቀረበ የድግሪ ማሟያ ጹሑፍ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከ1987-1990 ዓ.ም ከተሰበሰቡት 1990 የዘፈን ግጥሞች ውስጥ 200 ግጥሞችን በናሙናነት በመውሰድ በ4ቱ ዓመታት ታትመው ለገበያ ከቀረቡት ካሴቶች ውስጥ ከ1/10 በላይ የሚሆኑትን የሸፈነ ጥናታዊ ጹሑፍ ነው፡፡

የሰላማዊት ጥናት ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው የሊሻን ጥናት ጋር ቅርፅን መዳሰሷ ሲያመሳስላት አሁን ከሚደረገው ጥናት ጋር ደግሞ በዘፈን ግጥሞች ላይ ይዘት ትንተና ማድረጓ ጥናቱን አንድ ሲያደርገው ልዩነቱ አሁን የሚደረገው ጥናት አንድ አርቲስት በተለያዩ አመታት ያወጣቸውን አራት የዘፈን ካሴቶች ውስጥ የሚገኙትን እና የተመረጡትን የዘፈን ግጥሞች ብቻ የሚመለከት ሲሆን የሰላማዊት ስራ ግን ከ1987-1990 ዓ.ም በአራት ዓመት ውስጥ ታትመው በገበያ ላይ የዋሉትን የተለያዩ አርቲስቶች ስራ የዳሰሰ መሆኑ ጥናቱን ይለየዋል፡፡

4 ጎራው ሳልለው

"የአያሌው መስፍን ዘፈኖች የይዘት ትንተና እና የሴተኛ አዳሪዎች አተያይ" በሚል ርዕስ በ1984 ለዲማጽ የቀረበ ጥናታዊ ጹሑፍ ነው፡፡ ይህ ጥናት የአያሌው መስፍን ዘፈኖች ይዘት የተመለከተ ሲሆን በምዕራፍ አንድ ውስጥ ፍቅርን፣ ክህደትን፣ ጥላቻን...ወዘተ የመሳሰሉትን በማንሳት ተመልክተዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ሴተኛ አዳሪዎች በአያሌው መስፍን ዘፈኖች ላይ ያላቸው አተያይ በማለት ከዘፈኖቹ ውስጥ ሴተኛ አዳሪዎች ይወዷቸዋል የተባሉትን በመምረጥ ምክንያታቸውን በቃለመጠየቅ በማስደገፍ መረጃ የቀረበበት ጥናታዊ ጹሑፍ ነው፡፡

የጐራው ጥናት አሁን ከሚደረገው ጥናት ጋር የሚለየው በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ጉዳዩ ይመለከታቸዋል፡፡ ዜማውን ሲሰሙት ለነሱ የተዜመ ያህል የተለየ ስሜት የሚፈጥርባቸውን ሴተኛ አዳሪዎች ቃለ-መጠይቅ በማድረግ የቀረበ በመሆኑ

ከሚደረገው ጥናት ጋር ሲለያይ አብዛኛውን ጥናታዊ ጹሑፍ የሸፈነው ለዘፈኖቹ ግጥም ትንተና በመስጠት ላይ መሆኑ አሁን ከሚደረገው ጥናታዊ ጹሑፍ ጋር እንዲመሳሰል አድርጐታል፡፡

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በግጥም ላይ በርከት ያሉ ጥናታዊ ጹሑፎች ተደርገዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ አራቱ በተዛማጅ ጹሑፍነት የተመረጡበት ዋናው ምክንያት ከሌሎች ይበልጥ አሁን ለሚደረገው ጥናት ቅርበት አላቸው ብላ አጥኚዋ ስላመነች ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን አራቱ ጥናቶች የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን አንስተው የተዜሙ የዘፈን ግጥሞች የሚተነተኑ ሲሆኑ አሁን የሚደረገውም ጥናት በአንድ አርቲስት ስራ ላይ ያተኮር እንጂ የተለያየ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት የተዜሙ የዘፈን ግጥሞችን የሚተነትን ነው፡፡ አሁን ለማደረገው ጥናት ቀደም ብለው የተጠቀሱት ድምጾች ከሌሎች በተሻለ መልኩ ቅርበት አላቸው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የአርቲስት ፀጋዬ ስሜ ባህላዊ ዘፈኖች ግጥም ይዘት ትንተና

በዚህ ዕርስ ውስጥ የሚነሱት ጉዳዮች ሰፋ ያሉ ስሆኑ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ የዘፈን ግጥሞችን ወደ አማርኛ በመተርጎም ዘፈኑ ሊያስተላልፍ የፈለውን መልእክት ለመተንተን ሞክሪያለው፡፡ ከዛ ባሻገር በዘፈኖቹ ውስጥ የሚነሱትንና ብሔረሰቡ በቁሳዊ ባህልነት የሚጠቀምባቸውን ቁሳቁሶች አገልግሎታቸውን ለመግለጽ ሞክሬያለው፡፡

### 3.1. ጋብቻን በተመለከተ የተዜሙ

ጋብቻ የማኅበራዊ ኑሮ መሰረት አንደኛው ገፀታ ነው፡፡ በአበው አነጋገርም ጋብቻ በሦስት ጉልቻ ይመሰላል፡፡ በአገራችን ኢትዮጲያ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ብሄረሰቦች ባህላቸውን መሰረት ያደረገ የጋብቻ ስርዐቶችን ይፈፅማሉ፡፡ የጉራጌ ብሔረሰብም የራሱን የኑሮ ዘይቤና የሚተዳደርበትን ሕግና ደንብ መሰረት ያደረገ ጋብቻ ይፈፅማል፡፡ ቀደም ባለው ወቅት የጋብቻ ስርዐቱን ይፈፅሙ የነበረው መስከረም ወር ላይ ነበር፡፡ ነገር ግን ወቅቱ ዝናብ ጨርሶ የማያቆምበት እና በገጠሩ አካባቢ ደራሽ ውሃ የሚበዛ በመሆኑ ብዙ ሙሽራዎች በውሃ ሙላት ምክንያት በደራሽ ጎርፍ ይወሰዱ ነበር፡፡ በመሆኑም የጋብቻ ወሩን ለመቀየር ተገደዋል፡፡ የደጋው ሕብረተሰብ ሚያዚያ ላይ ሲያደርግ የቆላው አካባቢ ነዋሪ ደግሞ ጥር ላይ የጋብቻ ስነ-ስራታችውን ይፈፅማሉ፡፡ በዚህ የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ የተለያዩ ዜማዋች ይዜማሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ለትንተና ከተመረጡት የጋብቻ ዘፈኖች ውስጥ እንሾሽላና ዬዎሬ የሚሉት ዜማዋች የሕዝብ ሲሆኑ የተቀሩት ሁለቱ ደግሞ አርቲስቱ የጋብቻውን ስነ-ስረዓት አካሄድ እና ደንብ ወደግጥም በመቀየር ዜማ አላብሶ ያቀረባቸው ናቸው፡፡ የነዚህን የጋብቻ ዜማዎች ግጥም በቅደም ተከተል ለማየት ሞክሪያለው፡፡

#### 3.1.1 የሁዩባሶ

አርቲስቱ ይህን ዜማ የተጫወተው ብሔረሰቡ የሚያከናውነውን የጋብቻ አስተጫጫት ስርዓት የተጋቢዎችን ፍላጎት እና ስሜት የጠበቀ አለመሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ የዘፈኑን ግጥም በከፊል የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| አቢና እሚትዲ ላክሙቢም ባገር | - | እናት እና አባቴከገጠር ልከውብኛል |
| ቦርስከነም ምጣ ታትዋል ታታድረ | - | ናፍቀኸናል ሳትውል ሳታድር እንድትመጣ |

መሽማን ተብረግግ ታንኚ አደርኩም - ማታስቃኽ ሳልተኛ አደርኩ
ፈጠነው አለፈኪ ዛኝት ተነሳሁም - በጠዋት ተነስቼም ሄድኩ

አብዛኛው የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ ተወላጅ ከእርሻ ባሻገር በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሲሆን የንግዱን ሥራ የሚያከናውነው የገጠሩን ኑሮ በመተው ወደ ከተማ ወይም ከሚኖርበት ወደ ተሻለው እና ተሰርቶ ይታደግበታል ወዳለው ስፍራ በመጓዝ ነው፡፡ ይህን ግጥም የሚያንጎራጉረው ወጣትም ለስራ ያደገበትን ቀዬ ትቶ ቢሰደድም ቤተሰቦቹ እንደናፈቃቸው እና መጥቶ እናዲያያቸው በመጠየቅ መልዕክ ይልኩበታል፡፡ ወጣቱም ወላጆቹን ሄዶ እስከሚያገኛቸው ድረስ ጥሩውንም መጥፎውንም በማሰብ ምንገጥሞቸው ይሁን በሚል መጨነቁን ያመለክታል፡፡ በሚቀጥሉት ስናኞች ደግሞ ቤተሰቦቹ ጋር ሄዶ የገጠመውን ነገር እንዲህ ይገልፃል፡-

ጌተዋግባዲ ይፍት ፍላኂን ሁድኚ - እቤት ከመግባቴ የሚሆነውን ነገሩኝ
ታመድ ተሳር ንሳ ይጮኚ ባልኚ - ካመድ እና ከሳር የሚሻልክን ምርጥ ተባልኩ
እዲም ሳር ነሳሁም ገባሂ ተጌየን - እኔም ሳሩን በማንሳት ወደ ቤት ገባሁኝ
ዬብልኝ ነሰማይ ነዘም በይ ነብልየን - የሚሉኝን ልሰማ እና በዛውም ፍቃደኛ ልሆን

ከቤተሰቦቹ መልዕክት ተልኮበት የሄደው ወጣት የጠበቀው እሱ እንደገመተው ሳይሆን ሌላ ነበር፡፡ አባቱ በብሔረሰቡ ዘንድ ለመመረቅ አልያም ለመረገም የሚጠቀምነትን ሳር እና አመድ በመያዝ ከደጃፍ ተቀምጠው ነው፡፡ ወጣቱ ባደገበት ማኅበረሰብ ውስጥ ሳርም ሆነ አመድ ያላቸውን ትርጓሜ ያውቃል እና ከቀረቡለት ሁለት አማራጨች አንዱን በማንሳት ወደ ቤት ይገባል፡፡ ይህም በብሔረሰብ እምነት ሳሩን በማንሳቱ እርጥብ ሁን፣ የያዝከውን ይባርክልህ፣ ያሰብከው ይሳካልህ በማለት የሚመረቅበት ሲሆን አመድን ቢመርጥ ደግሞ እንደዚህ አመድ ብነን፣ የያዝከው አይበርክትልህ ዘር አይወጣልህ እንደሚባል ስለሚያውቅ ባሰባቸው መስማማቱን እና መፍቀዱን ለማመልከት ሳሩን ያነሳል፡፡ በመቀጠልም ወጣቱ ከማያውቃት የወደፊት ሚስቱ ጋር በሚመሰረተው ጋብቻ የተፈጠረበት ስሜት እንዲህ በማለት ይገልጻል፡፡

ወይ ነሻ ዬምከሬ ታይሻልኝ አትም - ይኑረኝ ልፈልግ እኔን ሳይጠይቁ
አሁትን ገዳደ ባልመኙ ፈጀነም - ጨርሰንልሀል አሁን ነው መዳሪያህ ጊዜህ አሉኝ

ፈጠነዉ ቁጭ ምበል ባይነብርቦም ጥፎ - በጊዜ መሰብሰብ መጥሮ ባይሆንም
ተሸላ ትትሽሌ ቅብ አልማን እርግፎ - አላዉቃት አታዉቀኝ ቅቤ የሌለዉ እርግፎ ነዉ

የነዚህ አራት ስንኞች መልዕክት ቤተሰቦቹ መፈለግ አለመፈለጉን ሳይጠይቁት የራሳቸዉን ፍላጎት ለማሳካት ሲሉ ብቻ ዘር ተቋጥረዉ የመረጡለትን ሴት ሳያዉቃት ሳታዉቀዉ አብረዉ በጋብቻ ተሳስረዉ እንዲኖሩ መደረጉን መጥላቱን እና በብሔረሰቡ ባህል እርግፎ በመባል የሚታወቀዉን ከእንሰት ተክል የሚዘጋጀዉን ምግብ ከሱ ጋብቻ ጋር በማያያዝ ገልፆታል፡፡ እርግፎ ቅቤ ከሌለዉ እና በደንብ ካልታሸ ጣዕም የለዉም፡፡ የኔና የሷም ጋብቻ የተመሰረተዉ ሳንተዋወቅ ሳንዋደድ፣ እሷ የኔን ፍቅር እኔም የሷን ፍቅር ሳላውቅ በመሆኑ የትዳርን ጣዕም አናውቀዉም የሚል ነዉ፡፡

ቀጥለን በምንመለከታቸዉ ስንኞች ሙሽራዉ በቆየባቸዉ ሳምንታት ውስጥ የተፈጠረበትን ሌላ ስሜት የሚገልፁ ናቸዉ፡፡

ኪያ በዛ ዬጦማሂ - እሷ እዛ ብቻዋን
ኸዲ በዚ ፈፉ □ሾሂ - እኔ እዚህ መከራ አየሁ
ናትመጣ የን ናይሆን ግቦ - እንዳትመጣ የተመቻቸ ነገር የለም
ኢኛቦ ዬለ ያስፈፈቦ - እግር የሚዘረጋበት የለ እንኳን የሚተኛበት

ከላይ የተጠቀሱት ስንኞች የዘፈኑ ርዕስ የሆነዉን ያሁዲ ባስ - የአሁኑ ባሰ የሚለዉን አስብ የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ ቀደምብለን ባየናቸዉ ስንኞች ዉስጥ የማያውቃትን ሴት እንዲያገባ በመገደዱ ማዘኑን ሲገልፅ ነበር፡፡ አሁን ግን አንድ አዲስ ነገር ተከስቶዋል ልጁ ያገባትን ሴት (ሙሽራዋን) ገጠር በሙሽራነት በቆየባቸዉ ሳምንታት ለምዷታል፡፡ በብዙ መልኩም አውቋታል፡፡ አዲስ አበባ ለስራ ተመልሶ ቢመጣም እየናፈቀችዉ ስራዉን መስራት አልቻለም፡፡ እንዳያመጣት እና አብረዉ እንዳይኖሩ የተመቻቸ ነገር የለም፡፡ የሆነዉ ይሁን ብሎ እንዳይቀመጥ ናፍቆቷ እያስቸገረዉ በመሆኑ ቀደመው ከነበሩት ችግሮች የአሁኑ የባሰ መሆኑን የገለፀበት ነዉ፡፡ አሁን የተከሰተዉም ሆነ ቀደም ብለን የተመለከትናቸዉ ችግሮች የተከሰቱት በተጋቢዎች ፍላጎት ሳይሆን ጋብቻው በወላጆች ምርጫ የተደረገ በመሆኑ ነዉ፡፡

### 3.1.2. እንሾሽላ

**እንሾሽላ፡-** የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ ጋብቻን አስመልክቶ ከሚያዜማቸዉ ዜማዎች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛዉ ነዉ፡፡ ብሔረሰቡ ስያሜዉን እንዴት እንደሰጠዉ ባይታወቅም የስያሜዉ የቀድሞ መጠሪ የነበረዉ እንሶስላ ሲሆን ይህም ሴቶች እግራቸዉን እና እጃቸዉን ለማስዋብ የሚጠቀሙበት ተክል ስያሜ ነዉ፡፡ እንሾሽላ እተባለ የሚጠራዉ የተለየ የጭፈራ ስርዓት የሚካሄድበት ቀንና የዘፈኑ መጠሪያ ነዉ፡፡ ይህ ስርዓት የሚካሔደዉ ጋብቻዉ እሁድ ከመፈፀሙ በፊት ቀደምብሎ አርብ ማታ ነዉ፡፡ ይህ የዘፈን ስርዓት የሚካሄድላቸዉ ለመጀመሪያ ጊዜ ጋብቻቸዉን ለሚፈፅሙ የብሔረሰቡ ተወላጆች ብቻ ነዉ፡፡

አብዛኛዉን የክስታኔ ጉራጌ ተወላጅ ከጋብቻዉ ቀን ይልቅ የሚናፈቀዉ ይህ ስርዓት የሚካሄድበትን እለት ሲሆን ለቀኑ ያላቸዉን ክብርና ለመድረስ ያላቸዉን ጉጉት ለማመልከት ቀኑን “የእንሾሽላ መአይዲ አያስላዬ” የእንሾሽላ ቀኔ አያድርሰኝ በማለት ለምሀላነት ይጠቀሙበታል፡፡ የዘፈኑ ግጥም ምን እንደሚመስል በሚቀጥሉት ስንኞች እንመለከታለን፡-

**ለሴቷ**

ትልባስ ነጠላሂ አንጮት ዬጨጭላ - ነጠላዋን ለብሳ ምንጣፍ ላይ ትቀመጥ
ዘመድ ዬስብስብም □ሹ □ፉት ዬበላ - ዘመድ ተሰብስቦ እንኳን ደስ ያለሽ ይበላት

የዚህ ዘፈን ግጥም መልዕክት በብሔረሰቡ ዘንድ ሴት ሙሽራ ምን ያህል ክብር እንዳላት ማሳወቅ ነዉ፡፡ ይህን ለማሳየት አንዷት ሙሽራ ከጋብቻ ቀኗ በፊት ወር ያህል ሲቀራት በብሔረሰቡ አጠራር ጥፍሯን ትቀፈፋለች ወይም የጥፍሯን ግማሽ ያህል ትቆረጣለች፡፡ ይህ የሚሆነዉ ምንም ስራ እንዳትሰራና የጋብቻዋ ዕለት አምሮባት እንድትታይ ሲሆን ከዚህ ባሻገርም ከባሏ ጋር በሚኖራት ግንኙነት ወቅት በጥፍሯ በመቧጠጥ እንዳትጎዳዉም ሲባል ነዉ፡፡ ሙሽራዋ ለዘመድ አዝማድ እይታ የምትቀርበዉ አርበሚታ ሲሆን ሙሽራዋ በሰዎች መሀል በምትወጣበት ወቅት በነጠላ ሚዜዎቹ ሸፍነዋት ብሔረሰብ ከእንሰት ቅርፊት በሚያዘጋጀዉ (አንጫት) ምንጣፍ ላይ እንድትቀመጥ ይደረጋል፡፡ የተሰበሰበዉ ቤተ ዘመድም ለሙሽራዋ ያለዉን አክብሮት እና መልካም ምኞት በጭፈራዉ መሃል ገብቶ ተሳታፊ በመሆን ይገልፃል፡፡

ቀጥሎ በሚቀርቡት ስንኞች የሙሽራዋ ተግባር ከራሷ አልፎ ቤተሰብን ምን ያህል እንደሚያኮራ የተገለፀበት ነዉ፡፡

አዋኘሽ ዬኻርልችን ጆላልደሽ - ዛሬ ይታይልሽ ቆንጆዉ ትንሹ ቤትሽ

የዉጣ አንጮት ዬጨጩየ ሻማ ስከር ያክላልቱየ - ምንጣፍ ወጥቶ ይነጠፍ ጣላዉም

በእንስራዉ ተሞልቶ ይቅረብ

ትቶና እሚት ዬድምቅባመ አቢሂም ዬዡ ዬቶናመ - እናት አምራ ደምቃ ትቀመጥ

አባትም ይይ ተቀምጦ

ዘመድ አዝማድ ዬስብስብም እንሾሽላ ዬበል ኩልም - ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ ሁሉም

ይበል እንሾሽላ

ዬዣ ገረድ በግፍተ አቢ እሚት ያትፊሰተ - ትታይ ልጅቷ መሀል ገብታ እናት አባቷን

ያስደስታቸዉ

አትም ምካት ታይስላባ በፉት በቅብ ዬላቀተ - ምንም ችግር ሳይደርስባት በወተት በቅቤ

ያደገች

ከላይ የቀረቡት ስንኞች ሶስት መልዕክቶች የሚያስተላልፉ ናቸዉ፡፡ የመጀመሪያዉ ሙሽራዋ ክብሯን በመጠበቋ፣ መልካም ስነ-ምግባር ያላት በመሆኗ፣ እናት አባቷን በቅንነት በማገልገሏ ሙገሳና ክብር እንደሚገባት የሚገልፅ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ደግሞ ለሙሽራዋ ሚዜዎች እና አብሮ አደግ ጓደኞች የሚያስተላልፈዉ መልዕክት አለ፡፡ እሷ ይህን ወግ ማዕረግ ማየት የቻለችው ክብሯን በመጠበቋ በመሆኑ እናንተም ይህን ማየት እንድትችሉ እና ለወግ ለማዕረግ እንድትበቁ ክብራችሁን ጠብቁ በማለት ለራሳቸዉ ከፍ ያለ ግምት እንዲሰጡና ብሔረሰቡ ስለ ሴት ልጅ ክብር ያለዉን አመለካከት እንዲያውቁ የሚያደርግ ነዉ፡፡ ሶስተኛ ሙሽራዋ ክብሯን በመጠበቋ ከራሷ አልፋ ቤተሰቦቿንም እንደሚያኮራና ይህ የአስተዳደግ ውጤቷን የሚገልፅ መሆኑን የሚነግረን ነዉ፡፡

ቀደም ሲል ለሴቷ ክብሯን በመጠበቋ የተዜመላትን ተመልክተናል፡፡ ለወንዱ ደግሞ ጀግንነቱን በቤት ዉስጥ ያለዉን አስተዋፅኦ የሚያሳይ እና ለወግ ማዕረግ በመድረሱ ወዳጅ ዘመድ መደሰቱን የሚገልፁ ስንኞችን እንመለከታለን፡፡

አምኘሽ ዬደ□የ ቢጤ ዘመድ በጌደያ - ዛሬ ዘመድ አዝማድ አንተ ቤት ተገኝቶዋል

መጠሙመ በስተተ ዬደርሰሙን □ገት ተ□ገተ - በሰላም መተዋል በተራ በተራ

ገብተዉ ይጨፍሩልክ

ሻማ ሰከር ሺለሙመ አቢ እሚት ቶነሙመ - እንስራ ሙሉ ጠላ ተዘጋጅቶ እናት እና

አባቱ ይቀመጡ

እንሾሽላ ይበል ሙነ እግዜር ነዚ ያስላነ - እንሾሽላ ይበል እግዚአብሔር ለዚ ስላደረሰን
ተጎሽም ጎሽ ገምያ ነ□ አቢ እሚት ያትፈሳ□ - ከወንድም ወንድ ጀግና ነክ እናት
አባትክን ያስደሰትክ
ተንሳም ድረስ በገዳደ አሁታለ ጎይ ጊንኽደ - ተነስተክ ጨፍር ዛሬ ጉልበትክ እያለ ወግ
ማዕረግክ ነዉን

የነዚህ ስንኞች ቀጥተኛ መልዕክት ዛሬ አለምክ ነዉ ተደሰት ጨፍር ይሄ ሁሉ የምታየዉ ዘመድ አዝማድ የተሰበሰበዉ ያንተን አለም ለማድመቅ ነዉ። ዛሬ የወጣትነት ጉልበትክ ሳይደክም እንዳሻክ ጨፍር ተደሰት የሚል ነዉ። ከዛ በመቀጠል የሚገልፀዉ በገጠሩ የሚኖረዉ የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ ኑሮ የተመሰረተዉ ባህላዊ በሆነዉ የግብርና ዘዴ ሲሆን ይህ የሚከናወነዉ ደግሞ በቤቱ አባወራ አማካኝነት ነዉ። ወንድ ልጅ በደረሰ ወቅት ግን የአባቱን ቦታ በመተካት እርሻዉን ይቀበላል፣ ቀዬዉን ይጠብቃል፣ ለእናት አባቱ መኩሪያ ይሆናል። ነገር ግን ልጃቸዉ ጎጆ ሊመሰርት መሆኑን ሲያዉቅ ቢደሰቱም ቀኑ እየተቃረበና ተለይቷቸው የራሱን ኑሮ ሊጀምር መሆኑ ሲገባቸዉ የሚሰማቸዉን የሀዘን፣ የፍርሃት እና የብቸኝነት ስሜት የሚገልፅም ነዉ።

### 3.1.3 ዬዎሬ

**ዬዎሬ፡-** የተሰኘዉ ዘፈን በክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ ጋብቻን በተመለከተ ከሚዜሙት ዜማዎች ውስጥ በሁለተኛነት የሚጠቀስ ነዉ። ይህ ዘፈን የሚዘፈነዉ አርብ ማታ እንሾሽላ ከተባለዉ የዘፈን ስነ-ስርዓት በመቀጠል ሲሆን ይህን ዜማ የሚያጀምሩት እናት፣ አባት ወይም ደግሞ እንሾሽላ እንዲል በመጨረሻ የተመረጠዉ ዘመድ ነዉ። ይህ ዜማ በሚዜምበት ወቅት ቀደም ብሎ እንሾሽላ ሲባል ሙሽሮቹ እንዲሸፈኑበት የተደረገዉ ነጠላ ተነስቶ ከሚዜዎቻቸዉ ጋር እንዲጨፍሩ ይደረጋል። የቅርብ የሆኑት ቤተዘመዶችም ሙሽራዎቹን በመክበብ ጭፈራዉን ያደምቃሉ። ይህ ዜማ የተለያዩ ግጥሞች ሊገጠሙበትና የተለያዩ ሰዎች ሊሞገሱበት ይችላሉ። ከነዚህም ዉስጥ ሙሽራዎቹን፣ እናትና አባትን፣ ዘርማንዘርን የሚቆጥሩ፣ ወዳጅ ዘመድን በተመለከተ የሚገጠሙ ይገኙበታል።

ይህ ዜማ ከአርብ ማታ በተጨማሪ እሁድ ጠዋት ሙሽሮቹ ከየቤታቸዉ በሚወጡበት ወቅት ወዳጅ ዘመድ እስከተወሰነ መንገድ ከበሮ በመያዝ የተለያዩ

ግጥሞችን በማውጣት እያዜመ ይሸኛቸዋል፡፡ የዚህን ዜማ ግጥም ለሴት እና ለወንድ የተባሉትን በመከፋፈል እንዲህ ቀርበዋል፡፡

**ለሴቷ**

ዬምሬ ዬበሏ ገረድ ደመቀባም - ዬዎሬ በሉላት ልጆት አምሮባታል

በንድር ዬሰበቱ ዬላቱዬ ኮነላም - በምድር የምታስበዉና የምትፈልገዉ ሆኖላታል

ዬዎሬ ዬበሏ ሀገር ከተት ዬሰማ - ዬዎሬ ይባልላት ሀገር ምድሩም ይስማ

አቢእሚት ያትፈሳት ከያትና መልካማ - እናት አባቷን ያስደሰተች እሷ ነች ቆንጆ ልጅ

ዬዎሬ ዬበሏ ሰምኪ ጢበቀትም - ዬዎሬ በሉላት ስሟን ጠብቃለች

ዬብሏ ቀይ ስማትም ስቢም አትፊሳትም - የሚሏትን ሰምታለች ሰዉም ተደስቷል

ከላይ የተገለፁት ስንኞች ቀጥተኛ መልዕክት ሙሽራዋ ከልጅነት ጀምሮ ታልመዉና ታስበዉ ለነበረዉ የጋብቻ ቀኗ ደርሳለች፣ ያሰበችዉና የፈለገችዉን አግኝታለች ይህንንም ለአገር ምድሩ ንገሩላት የሚል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ልጆች በሚያድጉበት ወቅት በመልካም ስነ-ምግባር ታንፀዉ እንዲያድጉ ቤተሰብ፣ ጎረቤት፣ እንዲሁም አብሮ አደግ ጓደኞች ያላቸዉን አስተዋፅኦ የሚያሳይ ነዉ፡፡ እነዚህ ማህበራዊ ሕይወት ዉስጥ ቅርበት ያላቸዉ ተቋማት እንደመሆናቸዉ መጠን ለመልካም ትዉልድ መፈጠር ያላቸዉን ይህ ነዉ የማይባ አስተዋፅኦ የሚያመለክት ነዉ፡፡

ቀደም ተብሎ በዘፈኑ ርዕስ ላይ እንደተገለፀዉ በዚህ ዜማ የተለያዩ ግጥሞች ሊባሉ እንደሚችሉ ተጠቁሞዋል፡፡ ቀጥሎ የምንመለከታቸዉም ስንኞች የሙሽራዋን የተወሰነ ቤተሰብ እያሞገሰ የሚቀጥርበትን ይሆናል፡፡

የማና በባሉ ጌሂ በሸሻሉ - የማናት ተብሎ ዘሯ ከተቆጠረ

ምድር በክስታኔ ኪያትና ዬበሉ - ይክስታኔ ልጅናት ይባል

አቢሂም ዝምነ ስዋተዉ ሙለነ - አባቱም ይሄ ነዉ ጎተራዉ የሞላ

እሚትኪም ልባምና የገረድ ቀንጡና - እናቷም ልባምና የሴቶች ቁንጮ የሆነች
ባለሙያናት

ሜቲዬም በሻሉ ሰባት ጌዋነ - አያቷን ሰባት ቤት ድረስ ቢጠይቁ

ቴውዱም ቲያበቀለ ያገሪን ችባነ - ተነግሮ የሚያልቅለት ያገር ምሶሶ ነዉ

ከላይ የተጠቀሱት ስንኞች የሙሽራዋን እናት አባት እንዲሁም አያቷን የሚመለከት ነዉ፡፡ ይህ ዜማ በሚዜምበት ወቅት ሙሽራዋ የአባቷን ብርቱነት የእናቷን ባለሙያነት የአያቷን የተከበሩ የሀገር አስታራቂነት ደጋግማ እንድታስብና ከነሱ በመገኘቷ የተለየ የኩራትና የደስታ ስሜት እንዲሰማት ያደርጋል፡፡

የዘፈኑ ግጥም ለሙሽራዋ አባትሽን ከጠየቁሽ ብርቱ ገበሬ፣ ጎተራዉ የሞላ፣ እንኳን ራሱን ሌሎችንም ማሳደር የሚችል ነዉ፡፡ እናትሽን ቢጠይቁሽ ይህቀረሽ የማትባል፣ ጠንካራ ለቤቷ ደከመኝን የማታዉቅ፣ ንፍገት የማይታይበት፣ በሙያዋ የሴቶች ቁንጮ ናት፡፡ አያትሽን ካሉሽ ተነግሮ የማያልቅለት የአገር ምሰሶ ነዉ፡፡ የተጣላን የሚያስታርቅ፣ መራቂ ሽማግሌ፣ በቀሉ የሚያድር መልካም ሰዉ ነዉ፡፡ አንቺ የተገኘሽዉ ከነዚህ መሆንሽን ንገሪ የሚል መልእክት ያስተላልፋል፡፡ ብዙጊዜ በብሔረሰቡ የጋብቻ ስነ-ስርዓት ላይ ይህ ዜማ በሚዜምበት ወቅት በሙሽሮችም ሆነ በወላጆች ላይ የሚፈጥረዉ የተለየስሜት አለ፡፡ በመከራዋ ላይ ይህን የመሰለ ቤተሰብ ትታ አዲስ ቤት ለመልመድ መዘጋጀቷን ስታስብ ሆድ ይብሳታል፡፡ ወላጆች ደግሞ ግጥሙን ማለት እስኪያቅታቸዉ ደድረስ በእንባ ሲቃ ምክንያት ይቸገራሉ፡፡ ይህ የሚሆነዉ ልጃቸዉ እቤት በነበረችበት ወቅት የነበራትን መልካም ነገር በማሰብ ዛሬ እነሱን ትታ ሌላ ቤት ልታደምቅ መሄዷን ሲያስቡ ሆድ ይብሳቸዋል፡፡ ይህም ለልጃቸዉ የነበራቸዉ ፍቅር ምን ያህል እንደነበር የሚያሳይ ነዉ፡፡

ቀደም ብለን የተመለከትነዉ ግጥም ለወንዱ ሙሽራም የሚባልለት ነዉ፡፡ ቀጥሎ የምንመለከተዉ ደግሞ ለሴቷ ክብሯን በመጠበቋ ስለክብሯ እንደተዜመላት ሁሉ ለወንዱ ደግሞ ጀግንነቱን እና ሌሎች ተግባሮቹን በማንሳት ይገጠምለታል፣ ይዜምለታል፡፡ ይህንንም ቀጥሎ በቀረቡት ስንኞች እንመለከታለን፡፡

**ለወንዱ**

ዬዎሬ ንበልን ነዚ ነዘሚኛ - ዬዎሬ እንበልለት ለዚህ ለመንድማችን
ዬሽኒ አገኝም ዎደድነሊም እኛ - የፈለገውን አግኝቶዋል እኛም ወደንለታል
አለንጋ ዋን በዘም በፈረስ በቶና - አለንጋዉን ይዞ ፈረስ ላይ ከወጣ
ዬሰላቦም ዬለ የፈረዝየን አና - ተወዳዳሪ የሌለዉ ጋላቢ ነዉ
ዬዎሬ ንበልን ንጡር ባናትኛ - የዎሬ እንበልለት በአናታችን ተሸክመን
ኢቲዡነም ማረግ ማለቂ ዘሚኛ - ማዕረግ አሳየን ትልቁ ወንድማችን

እነዚህ ስንኞች የተገጠሙት የቤት አንጋፋ (የመጀመሪያ) ልጅ በመልካም መንገድ ከተጓዘ ከሱ በታች ላሉት ታናናሾቹ ምን ያህል አርአያ እንደሚሆን ለማሳየት ነዉ፡፡ ሙሽራዉ ለዚህ ወግ ማዕረግ በመድረሱ መደሰታቸዉን፣ ምርጫዉን እንደወደዱለት እና ምንም የማይወጣለት ጀግና፣ ወደር የሌለዉ ጋላቢ እና ጠንካራ ሰራተኛ መሆኑን የሚገልፅበት ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሱ መልካም ቦታ መድረስ እኛም ስለነገ እንድናስብ እና እንደሱ ጠንካራና ብርቱ እንድንሆን አድርጎናል፡፡ ስለዚህ ደስታዉ ደስታችን መሆኑን አናታችን ላይ በመሸከም እንገልፅለት የሚል መልዕክት ነዉ የሚያስተላልፉት፡፡

### 3.1.4. ልሙ የኩንከ

**ልሙ**፡- የሚለዉ ቃል በማርኛ ትክክለኛዉ ፍቺ ይድገማቹ የሚል ነዉ፡፡ ይህን ቃል ብሔረሰቡ የተለያዩ ሁኔታዎችን በማስመልከት ይጠቀምበታል፡፡ ከነዚህም መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ ልጅ ለሚወልዱ ሙሽሮች ልሙ ዬኩንክም ደግማችሁ ዉለዱ ለማለት ይጠቀሙበታል፡፡ ሌላዉ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ልጁ ለሚድሩ ወላጆች ልሙ ዬኩንክም ደጋግማችሁ ዳሩ የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ይጠቀሙበታል፡፡ ቀጥለን በምንመለከተዉ ግጥም ዉስጥ ለእናትና አባት ልሙ የሚለዉን ቃል ከጋብቻ ጋር በማገናኘት እንዴት እንደተገለፀ እንመለከታለን፡፡

**ለአባት**

በጋመደ ታፊር በጠወረም ጊንዳ - ማረሻዉን ይዞ ከአፈር ከታገለ
ባባለትም ምድር ባረሰም በዘራ ታያዎና □ድጉት □ዳ - አሳምሮ አርሶ ከዘራ እዳ
አይቀመጥበትም
ሁሎ ተጥቤና ቁንጣ እንገለደ - ከጠዋት እስከ ማታ ቁምጣ እንዳደረገ
ቢሰበ ምዘላ ይዘኝ ጎይ አልደል ዎምሸዉ ብሩም ባላለየን - ስራ ለመሰራት ካሰበ
መንጋቱን እንጂ መምሸቱን እንኳን አያውቅም
ባደደም ቢበተ ወዘተዉ ባዣ - አጭዶ ከምሮ የልፋቱን ካየ
ታይቲክምም ታይሰጭ ዛትንጎይ ይገራ እናለ ቡዥቡዥ - ሳይበላ ሳይጠጣ ያኔ ይረካል
ሁሌ እንደኳተነ
ባኪደም ቢበተ ዬዉዛተዉ ባዣ - ወቅቶ አስገብቶ ጎተራዉ ከሞላ
ሂፍተዉ ይዝባበረም ሌላ ቃይ ይስቡ የካኒ አትሙ ቲሞላ - ፊቱን መለስ ቀለስ አድርጎ
ተመልክቶ ሌላ ነገር ያስባል የሱን ነገር ልብ ሳይል

ከለይ የተገለፁት ስንኞች ልሙ የሚባለዉ ቃል ለአባት በምን ምክንያት እንደተባለ የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ የግጥሙ ቀጥተኛ ትርጓሜ አባት ልጆቹን ለማሳደግ እና ኑሮዉን ለማሸነፍ የሚደርገዉን ትግል፣ ከራሱ ድካም ይልቅ ለነገ ምን ማኖር እንዳለበት በማሰብ እንዴት እንደሚጨነቅና ዛሬ ጎተራዬ ሞልቷል ልረፍ ከማለት ይልቅ ቀን ከሌት መኳተንን የሚመርጥ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ይህን የሚያደርገዉ ደግሞ ለልጆቹ፣ ለትዳሩ ሲል እንደሆነ የሚገልፁ ናቸዉ፡፡

በሌላ መንገድ ደግሞ ስንመለከተዉ አንድ ገበሬ መሬቱን ለእርሻ ሲያዘጋጀው ጥሩ ዘር እንዲፈራለት በቅድሚ መሬቱን በደንብ ያለሰልሰዋል፡፡ እርሻዉ ላይ ዘር ከዘራበት በኋላም እየተከታተለ ከአረም በመጠበቅ ለፍሬ ያበቃዋል፡፡ ጎተራዉ ሞልቶ ባየ ጊዜ የድካሙን ውጤት በማግኘቱ ይደሰታል፡፡ አባትም ደክሞ ለፍቶ ልጆቹን አሳድጎ ለወግ ማዕረግ ሲበቁ መሞገስ ያለበት እሱ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ሙሽራዋ/ዉ እዚህ የደረሱት በልፋትና በመልካም አስተዳደግህ በመሆኑ ወግ ማዕረጉ፣ ደስታዉ ይድገምክ በሌሎቹም ልጆችህ ወግ ማዕረግ እንድትደርስ እግዚአብሔር እድሜ ይስጥህ በማለት ልሙ ይኩንክ ይባላል፡፡

ቀጥለን በምናያቸው ስንኞች ደግሞ ልሙ የሚለዉ ቃል ለእናት እንዴት እንደተገለፀ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

**ለእናት**

በከረሰ ትናለ ትለግድት በጅኪ - ሆድ ውስጥ እንዳለ በእጇ እየዳበሰች
ቀነ ትቆጥሪ ብሩሙ ትጎጊ ምንታዥ ድረስ ቢንኪ - በአይኗ እስከምታየዉ ድረስ ጓግታ
ቀኑን ትቆጥራለች
ባኒጠስን ባገሮት ቡታዥ ያዥናትን - ሲያስነጥሰዉ ካየች በታየዉ ያያታል
ምስድብ ታበዘይ ትበድርም ትቂጢ ገና ታይሞት ትሞትለት - ምንም ሳይሆን ገና
በሕይወት እያለች ሳትሞት ትሞትለታለች
ሌማት ሙለ ከሸት ብተብ ብታበላ - መሶብ ሙሉ እንጀራ ሰጥታ ብታበላ
ቲመስላ ይገሮ ታይረብን ትሪቢ ትብሊ □ዲ አፈር ሙለ ነብላ - የሚጠግብ
አይመስላትም ሳይርበዉ ትራባለች ትላለች እኔ አፈር ልብላለት
ምዘላም በፈካ ይትመርይ ባለፈ - ለስራ ወይ ለመማር ከሄደ
ፈያ ይኖ ትትብል ኩል ጎይ ጥበትን አለመትኪም ሰርም ቲያርፉ - ሰላም ይመጣል
አትልም ሁል ጊዜ ጭንቀት ነዉ አፏም አያርፍላትም

ከላይ የተጠቀሱት ስንኞች ቀጥተኛ መልዕክት እናት ለልጇ ያላትን ጭንቀት እና ፍቅር ሆዷን እየደባበሰች አይኗን በአይኗ እስክታይና ልጇ በእቅፏ እስኪገባ መጓጓቷን እና መናፈቋን ይሰማት ይመስል የምታወራዉ መሆኑን የሚገልፁ ናቸዉ።

ከወለደች በኋላም ቢሆን ለልጇ ያላትን ፍቅር ለመግለፅ ሲያስነጥሰዉ ያየች እንደሆነ ካንተ በፊት እኔን በማለት በልጇ ንጥሳት ምክንያት እራሷን ምን ያህል አሳልፋ እንደምትሰጥ ያሳያል። በሌላ መልኩ ደግሞ ልጆችን የማሳደግ፣ የመንከባከብ ሃላፊነት በእናቶች ላይ የተጣለ መሆኑን ይገልፃል። ይህ ልጆች ከእናታቸዉ ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ በርከት ያለ በመሆኑ ይህ ወቅት በፍቅር እና በመልካም ስነ-ምግባር የታነፀ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት ስላለባት ብርቱ ድካም እንደሚገጥማት ያመለክታል። የልጅነት ጊዜውን ጨርሶ ለወግ ማዕረግ በሚበቃበት ወቅት ያልተዘራ አይበቅልምና እናት ከልጇ ጋር በነበራት ቆይታ ያበረከተችዉ ትልቅ አስተዋፅኦ ለልጇ እዚህ መድረስ መሰረት በመሆኑ ይህ ወግ ማዕረግ ለሙሽራዉ /ዋ/ ሳይሆን የሚገባት ለእናት ነዉ በማለት ልሙ ይኩንሽ ደጋግመሽ ዳሪ በማለት መልካም ምኞታቸውን ይገልፃሉ።

## 3.2. ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች በተመለከተ የተዜሙ

በዚህ ርዕስ ውስጥ የሚተነተኑት ዘፈኖች የተለያዩ እርዕሰ ጉዳዬችን የሚመለከቱ ሲሆኑ እነዚህ ዘፈኖች ብሔረሰቡ በተለያዩ ወቅቶች የሚጠቀሙበትን ስነ-ቃሎች አካተው የያዙ ናቸው። ከነዚህ ስነ-ቃሎች ውስጥ በአሁን ወቅት እየተባሉና እየተከወኑ የሚገኙ ሲኖሩ ጨርሰው የተረሱና የጠፉም ይገኙበታል። እነዚህ ስነ-ቃሎች በዜማ የቀረቡት ይዘታቸውን እና የሚያስተላልፉትን መልእክት ሳይለውጡ ነው። የእነዚህ ዘፈኖች ግጥም በቅደምተከተል እንዲህ ተቃኝተዋል።

### 3.2.1. ወሴባሳ

የእድሜ ባለፀጎች እንደሚሉት ወሴባሳ የሚለው ስነ-ቃል በክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ ዘንድ ለነውር ወይም በብሔረሰቡ ውስጥ አዲስና ያልተለመደ ነገር ሲታይ የሚጠቀሙበት ስነ-ቃል እንደነበር ነው። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ሰርዓቱም ሆነ ስነ-ቃሉ በብሔረሰቡ ዘንድ ጨርሰው ተረስተዋል። ይህ ስነ-ቃል ይባል የነበረው የተለያዩ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ወቅት ነበር። ከነዚህም መካከል አንዷት ሴት ባሏ ለረዥምም ጊዜ በዘመቻም ሆነ በስራ አጋጣሚ ቆይቶ ሲመለስ ከሌላ ወልዳ ከጠበቀችው፣

የሰውን ነፍስ በግፍ ለገደለ፣ የሰውን ቤት ንብረት ላቃጠለ፣ ያልተፈጠረን ነገር ተፈጠረ ብሎ በወሬ ትዳርን፣ ሀገርን፣ መሀበራዊ ህይወትን ለሚያናጋና ለሚበጠብጥ ሰው ወሴባሳ ይባላል፡፡ አርቲስቱም ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የሆነውን ወሬን በመምረጥ እንዲህ ይገልፀዋል፡፡

ሸንጎ ተምን ዋለ በበሉ - ሸንጎ ምን ላይ ዋለ
ኸከሌ ገደሉት ኸከሌ አገዱት ምድር አካፈሉት - እከሌ ተገደለ እከሌም ታሰረመሬትም ተካፈለ
አገርሽ ምን ባለ በምንዋለ - አገሬው ምን አለ በምን ዋለ
አትም አልዘበረ ከሽትም አልበላ ሂኖ እናደረ - ምንም አልመለሰም ምግብም አልበላ እንዳደረ አለ

ከላይ የተጠቀሱት ስንኞች የሚያስተላልፉት መልዕክት የወሬ ሱስ ያለበት ሰው የተከበሩ የአገር ሽማግሌዎች ተሰብስበው ያስማሙትን ጉዳይ ለወሬ ከመቸኮሉ የተነሣ እከሌ እና እከሌ በመሬት ጉዳይ ተጣልተው አንዱ ተገደለ ገዳዩም ታሰረ ሽማግሌዎቹም መሬቱን አካፈሉ ብሎ ያወራል፡፡

አገሬው ይህን ሰምቶ ምን አለ ሲባል በጉዳዩ ላይ ምንም አላለም ጉዳዩን እስኪሰማ ድረስ ምግብ በአፉ አልገባም ብሎ ያወራል፡፡ ይህ የሚያሳየው ሽማግሌዎች አስማምተው ያስሩትን ጉዳይ በወሬ ለመፍታት ሲጥር ወሴባሳ ብለክ ወሬውን አጥላለበት የሚል መልዕክት ነው የሚያስተላልፉት፡፡

ቀጥሎ በምንመላከታቸው ስንኞች ደግሞ መጥፎ ወሬ እየሰማ ያስቸገረን ጆሮ እንዲህ በማለት ይወቅሱታል፡፡

ኽረተው እንዝን ኬር ቃይ ስማ - እባክህ ጆሮ ጥሩ ነገር ስማ
መጥረም ፈያው አጥመማ - መርጠህ ጥሩ ውን ብቻ ስማ
ባልኮነ ፈያሆም ፄድፍንን - ካልሆነ ደህና አድርጎ ይድፈንክ
ተፈያ ጥፋዩ ባሸንን - ከጥሩው መጥፎውን ከወደድክ

ከላይ የተመለከትናቸው ስንኞች አንድ ሰው ወሬ እየሰማ ያስቸገረውን ጆሮ እንዴት እንደሚያማርር የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይህውም እባክህን ጥሩ የሆነውን መርጠክ

ስማልኝ፡፡ የሚጠቅምህን መርጠክ መስማት ከጠላህ እና መጥፎውን ከወደድክ ለኔ አጠቅመኝም እና ብትደፈን ይሻላኛል የሚል እሮሮ ነው የሚያሰማው፡፡ ይህ የተባለበት ምክንያት ወሬ ማህበራዊ ኑሮን፣ ትዳርን፣ እንደሁም ከነአባባሉ "ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው" የሚለውን በማሰብ ሀገርንም ጭምር ስለሚያናጋ ይህ የሚሆነው ጆሮ ወሬ በመስማቱ ስለሆነ መጥፎ የሚሰማው ጆሮ ቢደፈን /ባይሰማ/ ይሻላል የሚል ነው፡፡

ቀጥለን የምንመለከተው ወሬ የሰዎችን ጆሮ እና ቀልብ ለመሳብ ምን ያህል ተጋኖ እንደሚወራ የሚያሳይ ነው፡፡

ባሉትን ዚ ተዛ ቃኖትን - ተብሎ ተነገረ ይህ ያሆነ
በጆረ ምድር አረሱትን - በደሮ ምድር ታረሰ
በሰሞ በእንዛን ባጥመሞ - ከተሰማና ጎሮ ካዳመጠ
ያርጡትን ቀስላ በገንዘሞ - እንጫት በመፍለጫ ይቆረጣል

ከላይ የተመለከትናቸው አራት ስንኞች የሚያስተላልፉት መልዕክት ብሔረሰቡ እንደ ስርዓቱና እንደ አኗኗር ዘይቤው የተለያዩ ጉዳዮች የሚገለገልባቸዉ ቁሳቁሶች አሉት፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከላይ በቀረበዉ ግጥም ዉስጥ የተጠቀሰዉ እና በብሔረሰቡ አጠራር ሰንዳ እየተባለ የሚጠራዉ ስለት አንዱ ነዉ፡፡ ይህ ቁስ ብሔረሰቡ እንሰት ለተባለ ተክል መቁረጫነት የሚገለገልበት ሲሆን ወሬግን እንሰት በሰንዳ መቆረጥ ቀርቶ ብሔርሰቡ ለእንጨት መፍለጫነት እና ለአጥንት መቀጥቀጫነት በሚጠቀመው መሳሪያ እንሰት ተቆረጠ በማለት ያወራል፡፡ የብሔረሰቡ ቁሳዊ ባህል የሆነውን መሣሪያ ያለ አገልግሎት በማዋል ተደረገ ብሎ ሲያወራ በማንነትህ ኮርተህ የኔ ብለህ የምትጠቀምበትን ቁሳዊ ባህልህን ያሳጣሃልና ወሬ ባሳ በለው የሚል ነው፡፡

ቀጥሎ የምንመለከታቸው ስንኞች በቤተሰብ ላይ ወሬ የሚያስከትለውን ችግር የሚያሳዩ ሲሆኑ ከላይ የተሰጠቀሱትንም ሆነ አሁን የምንመለከታቸው ነውር የተባሉ ድርጊቶች ሲታዩ እንዴት ስርዓቱ እንደሚከናወን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ቀኒ ባልመጠረም ተምሸተው ባልዩና - ቀኑን መርጦ ከሚስቱ ጋር ካልተቀመጠ
ጉባኒን ያጠልሰም የሰብጌ ባቀና - የራሱን አጥፍቶ የሰው ቤት አበጀ
ምሽትም ጌ በሳተት ሚዳ በጫመና - ሴትም ቤቷን ትታ ውጪውጪ ካለች

ዘ ባሉት ዛ ባሉት አመል በኮነና - ይህ ሆና ያሆነ እያሉ ማውራት አመልከሆናት

አያገቾቃይ ባገቾ አይኮን ቃይ በኮነ - የማይታይ ነገር ከታየ የማይሆን ነገር ከሆነ

ዬስባከሩም ጎይ በሽ ባሉት ታይፈጀነ - ቅጥል ታቀነጣጠስ ወሬ ሳይመረከን

ዚባዥር ታዩቅስ ዬጠሩም በሰንሳ - ቃሀ ስታየ ቢዋላ ሳይጠበቅ ተሸክመን በቃሬዛ

ዬቁሙም ባገደል ዬበሉዋሴ ባሳን - ገደል ላይ በመቆም ወሴባሳ ይባል

ቀደምብለን ባየናቸው ስንኞች ወስጥ የሚተላለፈው መልክት አባወራ ወሬ እንዲሆን እያለ ማውራቱን ትቶ ቤቱን መስሎ መኖር ካቃተው እና የራሱን ቤት በወሬ ምክንያት አፍርሶ የሰው ቤት ገመና በመከታተል የራሱን ቤት ካፈረሰ ሴቷም የሴት ልጅ ተግባር የሆነዉን ቤቷን ማለት ትታ ወሬ በመቋጠር ከአንዱ ወደ አንዱ የምትል ከሆነ ይህ ሆነ ያ ሆነ ማለት አመል ከሆነባት ይህ ከብሔረሰቡ ስርዓት ውጪ ነዉና ወሴ ባሳ መባል አለበት የሚል ነዉ፡፡

ስርዓቱ እንዴት እንደሚከናወን በተመለከተ በግጥሙ ዉስጥ እንዲህ ተገልፆዋል፡፡ የማይሆን ነገር ሆኖ ከታየ ወሬ አገራችንን ከማጥፋቱ በፊት እርጥብ የሆነ ቅጠል ቀነጣጥሰን በቃሬዛ ተሸክመን ለኛ እንደማይጠቅም በድን እሬሳ አስበነዉ ወደኛ ዳግም ተመልሶ እንዳይመጣ ገደል አፋፍ ላይ በመቆም ቅጠሉን ወደታች በመወርወር ወሴ ባሳ ነዉር መጥፎ ነገር ዳግም ወደኛ አትመለስ በማለት ቃሉን ደጋግመዉ በመጥራት የያዙትን ቅጠል በየተራ ወደ ገደሉ ጥለዉ ይመለሳሉ በማለት ተገልጿል፡፡

### 3.2.2. ኬር ይኽ፧ን

**ኬር ይኽ፧ን፡-** የሚለዉ ቃል ትክክለኛዉ የአማርኛ ትርጓሜዉ ሰላም ይሁን የሚል ሲሆን ለሰዉ ልጆች አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መሀከል ሰላም አንዱ እና ዋነኛዉ ነዉ፡፡ ሰላም ሲኖር ወጥቶ መግባት፣ ወልዶ ማሳደግ እና ለቁም ነገር ማብቃት፣ ተምሮ ቤተሰብን፣ አገርን መጥቀም የሚቻለዉ ሀገር ሰላም ሲሆን ብቻ ነዉ፡፡ ብሔረሰቡ ይህን ስነ-ቃል በተለያዩ ስነ-ስርዓቶች ላይ ይጠቀሙበታል፡፡ ከነዚህም መካከል ጋብቻን፣ ምርቃትን፣ እርቅን እና ሌሎችንም ጉዳዮች በተመለከተ በሚካሄድ የምርቃት ስነ-ስርዓቶች ላይ ቃሉን ደጋግሞ በመጥራት አሜን ይሁንልን በማለት ምርቃቱን የሚያሳርጉበት ቃል ነዉ፡፡

ቀጥለን የምንመለከተዉ የዘፈን ግጥም የሀገር ሰላምን በተመለከተ የተገጠመ ነው፡፡

ያዋሩዩ ምን ዬኮን ዩስሞዩም ምን ዩሁን - የሚወራዉ ምን ይሁን የሚሰማዉ ምን ይሁን

ዩሚርቂም እግዜር ዬኩን ዩትሚሪቅም ሰብ ዬሁን - የሚመርቀዉ እግዜር ይሁን የሚመረቀዉ ሰዉ ይሁን

አገር ከተቲ በሙለ ሰኛት ዬምብር በምድረ - በአገራችን ሁሉ ባታ ሰላም ይሁን

ዚ ያዠዩ ብልቃት ያትፈሲ በሙለ - ይህ ሁሉ ደስታ የሚታየዉ

ቢለብሱም ቢደንቁም አገር ስኛት ባለን - ቢለበስ ቢጌጥም አገር ሰላም ሲሆን ነዉ

ፈያ በወረሩም ያጥማማ ባለ - ጥሩ ነገር ሲወራ የሚያደምጥ ካለ

ቲፍትየን አልደበል ተፎለየን ዬለ - ወደፊት ነዉ እንጂ ወደ ኋላ ማለት የለም

ኩልም ዩኪተልት ዬዝበርም ዬለ - ሁሉም ይከተለዋል የሚመለስም የለም

ከላይ የተመለከትናቸዉ ስንኞች የሚገልፁት የምርቃት ስርዓቱ የሚካሄደዉ በሽማግሌዎች ሲሆን በሚመርቁበት ወቅት ምርቃቱን የሚያደርገዉ እግዚአብሔር ነዉ ምርቃቱን የምንቀበለዉ ደግሞ እኛ ነን በማለት አገራችንነ ከጫፍ - ጫፍ ሰላም ያድርግልን የምናየዉ ደስታና ፍስሃ የተገኘዉ አገራችን ሰላም ስለሆነ ነዉ። ጥሩ ሲወራ የሚያደምጥ ካለ ለሀገር ጥሩ ነገር ሲታሰብ እኔም አለዉ ከተባለ አገር ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ አትልም። እግዜር ምርቃታችንን ይቀበለን ምኞታችንን ያሳካልን ብለዉ ሽማግሌዎች ምቃታቸዉን ሲያሳርጉ ሌሎቹ ታዳሚዎች ደግሞ እጆቻቸዉን በመዘርጋት ኬር ኬር ኬር ዬሁን በማለት 3 ጊዜ ቃሉን ከጠሩ በኂላ እጃቸዉን ይሁን ይደረግልን በማለት ይስማሉ። ይህም ብሔረሰቡ ለሽማግሌዎች ምቃት ምን ያህል ግምት እና አክብሮት እንዳለዉ የሚያሳይ ነዉ። ሽማግሌ ሲመርቅ ኬር ዬሁን ብሎ የተቀበለ ሰዉ ሁሉም ነገር እንደሚሳካለት እና ቀና መንገድ እንደሚገጥመዉ ይታመናል። ብሔረሰቡ ይህንን ቃል በተለያዩ ስርዓቶች ላይ ይጠቀማቸዋል።

በመቀጠልም የተገለፁት ስንኞች እንዲህ በማለት ኬር ዬሁን የሚለዉ ቃል ይላሉ፡፡

ኽደሽ ባገርዲ አት ዬኖ ብላተ - እኔ አገር ዉስጥ አንድ ብላት አለ

በሙሊ አንገዶ ዬሲር ሞፈን ባለ - ከበርት ሙሉ ከብት የሚበጠብጥ ካለ

መሴር ዬዋ ቀለም ጠማኂን ያግዱተ - እንጨት ተመቶላት ብቻዉን ይታሰራል

በኳም ባልኮነለ ፈያ ዩዎቅጡተ - በሱም ካልተስተካከለ ይወቀጣል (ይኮላሻል)

ኗም ዩሸክትትን ኬርም ኮንለተ - እሱም ይስተካከላል በረቱም ሰላም ይሆናል

ከላይ ከተጠቀሱት ስንኞች ሊተላለፍ የተፈለገዉ መልእክት እያንዳንዱ ብሔረሰቡ የራሱ የሆነ የሚተዳደርበት ሕግና ደንብ ይኖረዋል፡፡ ማንኛዉም የማህበረሰቡ አባል በብሔረሰቡ መሀል ካደገ ሕግና ደንቡን ጠንቅቆ ማወቅ አለበት፡፡ ነገር ግን ግዴታዉን ሳያውቅ ቀርቶ ሕጉን ቢጥስ በመጀመሪያ እንዲመከር እና ይቅርታ እንዲጠይቅ ይደረጋል፡፡ ስህተቱን የሚደጋግም ከሆነ ብሔረሰቡ ከሚያከናውናቸዉ መህበራዊ ጉዳዮች በማገድ የብቸኝነት ስሜት እንዲሰማዉና ጥፋተኝነቱ እንዲታወቀዉ ያደርጉታል ያም ሰዉ ከጥፋቱ ይመለሳል፡፡ ይህ ሆኖ መመለስ ካልቻለ ይህ ሰዉ አንድ ችግር ገጥሞታልና የማህበረሰብ አባል በመሰብሰብ ኬር ዬኹን ወይም ወደቀድሞ አንተነትህ ይመልስህ በማለት ሰላም እንዲበዛለት ምርቃቱ ይካሄድለታል፡፡ ከዚህ ባሻገር በግጥሙ ላይ እንደተጠቀሰዉ በጉራጌ ብሔረሰብ ውስጥ አንድ የሚደረግ ብልሀት አለ ይሄዉም በረት ሙሉ ከብት ያለዉ ሰዉ አንዱ እየበጠበጠ ሌሎቹን ሰላም ከነሣቸዉ የሚደረግ ዘዴ አለ፡፡ በመጀመሪያ ከብቱን ከሌሎቹ ለይቶ በማሰር እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡ ይህ ተደርጎ ፀባዩ ካልተለወጠ በብሔረሰቡ አጠራር ዬዋቅጡት ይኮላሻል ያኔ የተሰማዉ የጥጋብ ስሜት ይበርድለታል በረቱም ሰላም ይሆናል በማለት ገልፃል፡፡

### 3.2.3 ዬሻልቢ

**ዬሻልቢ፡-** የሚለዉ ቃል ቀጥተኛ ትርጓሜ ይወቅብኝ በማለት ሲሆን የብሔረሰብ ተወላጅ የሆኑ አዛውንቶች ቀደም ባለዉ ወቅት ብሔረሰብ ቃሉን ይጠቀም የነበረዉ የተደበቁ ግን ያልታወቁ፣ የታወቁ ግን የተደበቁ ሚስጥሮችን ለመግለፅ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ስነ-ቃሉ በማንኛዉም አጋጣሚ እንደማይሰማና ጨርሶ እንደጠፉም አክለዉ ይገልፃሉ፡፡ ቀጥሎ በምንመለከታቸዉ ስንኞች ውስጥ ቃሉ ከጀግንነት ጋር በማያያዝ እንዴት እንደተገለፀ እንመለከታለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| በምባም ጎይ ደብር በገደለ አንበሳ | - | ጫካ ገብቶ አንበሳ ከገደለ |
| ባጀም ጎይ ዘሚኗን ባዣረገ ኧሪሳ | - | ወንድሙን ገድሎ እሬሳዉ ከተራመደ |
| በሰበር ውደማ በኪሪ ረሃኘ | - | የእህል ጎተራ ከሰበረ በረት ቆፍሮ ከገባ |
| ቅንን በሰጠም ጎይ የምሸት ባልኘ | - | ቀን ተደብቆ ማታ ካልተኛ |
| ኧጣይ ባገዳቦ በገንቦ በፈታ | - | የታሰረ በግበ ከታሰረበት ፈቶ ከሄደ |

በተጋን በሳጠም ጀራረ በነታ - እንስት ዉስጥ ተደብቆ ዶሮ ከሰረቀ

ያረደኒ ሞፈን በሳይስት በፈጀ - ያሪደዉን ወይፈን በስስት ቀን ከጨረሰ

ከላይ የተገለፁት ስንኞች የሚገልፁት አንድ ወንድ ጀግና የሚባለዉ አንበሳ ስለገደለ፣ የወንድሙን እሬሳ ስለተራመደ፣ የሰዉ በረት ቆፍሮ ገብቶ ከብቶች ስለነዳ፣ ቀን ቀን ተደብቆ ጨለማን ተገን አድርጎ ስለዘረፈ፣ ያረደዉን ወይፈን በሶስት ቀን በልቶ ስለጨረሰ አይደለም፡፡ ይህን ስላደረገ ጀግና የሆነ፣ ሰዎችን የረታ፣ ክብር ያገኘ ከመሰለዉ ስህተት ነዉ፡፡ ይሄኔ በሱ ቤት ያለሱ ወንድ የሌለ መስሎት ወንድ መሆኑ ነዉ፡፡ ስለ ዘረፈ፣ ስለገደለ ጀግና የሆነ ከመሰለዉ አለመሆኑን ማወቃችንን ይወቅ፡፡ የሚል ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ የሰዉን ነገር በመመኘት ሲቀጥልም በመዝረፍ የራስ ማድረግ ለጊዜዉ የሚያስደስታቸዉ ቢኖሩም ነገ ሀቁ ሲወጣ በስራቸዉ ያፍራሉ ጀግና አለመሆናቸው ሲታወቅ አንገታቸዉን ይደፋሉ፡፡ ጀግንነት ከፈለጉ ማግኘት የሚቻለዉ በመጣር፣ የሰዎች ከመመኘት የራስን ለማግኘት በመልፋትና እራስን ከሌሎች ዝቅ አድርጎ በመስራት ነዉ የሚል መልእክት ያስተላልፋል፡፡

በመቀጠልም ጀግና የሚባለዉና ጀግንነቱ የሚታወቅለት ወንድ የሚያደርገዉ ይህንን ነዉ በማለት በሚቀጥሉት ስንኞች እንዲህ ተገልፀዋል፡፡

ለዲ ያሊዬ ዚ የሻልን የጎሽ ዎልድ ያዥቦ - ለኔ የታየኝ ይሄ ነዉ የሚያውቅ ወንድ
ልጅ የሚታይበት

ላገር ለሰብ ሂሰብ ፍያ አይቀብጥቦ - ለአገር ለሰዉ የሚያስብ ጥሩ ነገር የማይታጣበት

ምካት ሺልትሞ በምድር ያለድርስ - በምድር እስካለ ድረስ ችግርን የሚያውቅ

ቢሞትም ይዙግዱት ዎዘላጊን ቲደበ - ቢሞትም ይታወሳል ስራዉ ይወራለታል

ከላይ የተገለፁት ስንኞች የሚያመለክቱት ወንድ ልጅ ጅግና ነዉ የሚባለዉ መልካም ምግባር ሲኖረዉ፣ ሰዎችን የማያስከፋ ከሆነ፣ የራሱን እንጂ የሰዉን የማይፈልግ፣ በላብ የሚያድር፣ መልካም ነገሮችን በማድረግ በሰዎች ዘንድ ጥሩ ስም ያለዉ፣ የሰዎችን ችግር እንደራሱ የሚመለከት፣ እራሱ ቢቸገርም ችግሩን ለመፍታት ብልሀተኛ የሆነ ነዉ ወንድ እና ጀግና የሚባለዉ፡፡ አንድ ሰዉ ጀግና የሚባለዉ አንበሳ ስለገደለ ብቻ አይደለም በሰራዉም ጀግና ተብሎ ሊወደስ ይችላል፡፡ ከላይ የተገለፁትን የሚተገብር ነዉ ጀግናና ወንድ የሚባለዉ በርግጥም ይህን የሚደርግ ከሆነ የወንዶች ወንድ ነዉ በማለት ይገልፀዋል፡፡

### 3.2.4. ለፌ

**ለፌ**፡- የሚለዉ ቃል ብሔረሰቡ ፅሑፍ ባልነበረበት ወቅት የተለያ ጉዳዮችን ለማስፈፀም ቃል ለመግባት የሚጠቀመዉ ስነ-ቃል ነዉ። ይህን ቃል ብሔረሰቡ ከሚጠቀምባቸዉ ተግባሮች መሀከል አንድ ገበሬ እርሻ ላይ በህብረት (ደቦ) ስራ ለመስራት ሲወሰን ሰዉ እንዲመጣ ቃል በማስገባት ስራዉ እንዲሰራ ለማድረግ፣ አንድ ሰዉ ብድር ተበድሮ ለመመለስ በዚህ ቀን አመጣለው በማለት ቃል በማስገባት በጊዜዉ እንዲመልስ ለማድረግ እና ሌሎች ጉዳችም እንዲፈፀም ለማድረግ ቃሉን ይጠቀሙበታል። ቀጥለን በምንመለከተዉ የዘፈን ግጥም ውስጥ ስራህን ጠንክረክ ለመስራት ቃል ግባ የሚል ትርጓሜ የያዘዉን ግጥም ቀጥለን እንመለከታለን።

ነገ ሲስተ አትበል ሂኖሆ ማኔው አትበል - ዛሬ ነገ አትበል ሰው አለ አትበል
በጌ ጋራ ያለ ያንብሊ ምድር - ከቤት ጓሮ ያለዉ ጎመኑ መሬት
ምን ይልገዴ ባሎ ያልዩ ዘንድር - ዘንድሮ ምን ነካኝ ብሎዋል
በወርድክ በታተ በወጣኽ ገገራ - ወደታች ብትወርድም ዳገትም ብትወጣ
አትም ታመጣልከ ያቢደን አደራ - ማንም አይመጣልክም ያባት አደራ ነዉ
ቢጋ ውሽጣ ያለ የቆለጫ አርፋ - በውሃ ውስጥ ያለው የንቁራሪት ምራቅ (አረፍ)
ዚ እማ ባልስገርከ ሆንብርም ቢደፋ - ይህንን ካልቀየርክ መኖር ቢቀርብክ
ለፊበል ለፊ በል ለሀገርዶ - ቃልግባ ቃል ግባ ለሀገርክ
አሁናም ጎይ ተገና ተመካን ባይደክ - ልጅክ እንዳይቸገር አስቀምጠክለት እለፍ
ለፊ በል ለፊ በል ለጌደ ቲመካን አቢደ ቲመካና እሚትዶ - ቃል ግባ ቃል ግባ ለቤትህ
እንዳይቸገር አባትህ እንዳትቸገር እናትህ

ከላይ የተገለፁት ስንኞች የሚያስተላልፉት መልእክት ስራ ለመስራት ሰው አይኝ አላየኝ አትበል የምትሰራው ለራስክ ስትል ነዉ። ዝምብለክ ወደላይ ወደታች በማለት ጊዜህን አትፍጅ ይህ መሬት ያባትህ ድርሻ ነው። አንተን ለማሳደግ ብዙ የለፋበት የታገለለት መሬት ነውና ዛሬ አንተ ባለተራ ስትሆንክ መሸሽ የለብህም አንተ አልሰራም ብልክ የናከውን ማንም ሊሰራልክ አይችልም። ከዚህ ባሻገርም በገጠሩ አካባቢ ውሃ የሚጠቀሙት ከጉድጓድ ውስጥ ነው። እዚህ ጉድጓድ ውስጥ ደግሞ ብዙ ጊዜ እንቁራሪቶች ስለለሚኖሩ ምራቃቸውን ይተፉበታል ውሃውን ልትቀዳ ስትል ያንን አረፋ ካላፀዳክ ውሃውን አትጠቀምበት ይህን ሳታደርግ ውሃውን ከቀዳከው ግን ስንፍናህ ምን ያህል እንደበረታብህ ያመለክታልና ከዚህ የባሰ ነገር ሳይመጣ ቃል ግባ ለሀገርክ

ቃል ግባ ለልጅህ ዛሬ ሰርተህ አስቀምጠክለት ለማለፍ ቃል ግባ እናት አባትህ ደክመው ስትጦራቸው ያንተን ችግር እያዩ እንዳይሳቀቁ ሰርተህ ጎተራህን ለመሙላት ቃል ግባ የሚል መልዕክት ነው የሚያስተላልፈው፡፡ ቀጥለን የምንመለከታቸው ስንኞች ደግሞለስራ እንዲበረታታ የሚያነሳሱ ናቸው፡፡

እዲ ባልባሎ ነው የብሎ ነው ዘረ - እኔ ትልቅ ነኝ የትልቅ ስው ዘር

አገርም ሞላዬም እገባው ዘንድረ - አገር አለኝ ዘንድሮ እገባለው

ሆበሊ ግፋርም ታይታለፋ ሻልቦ - ማለቱን ተውና ሳያልፍብክ እወቅበት

ነገሌላቀንን አሁተውጋገትቦ - ነገ ሌላ ቀን ነው አሁን ከተማርበት

ነባይባይዲ ምን አሆናሁለ - ለልጅ ልጅ አሁን ምን አስቀምጥለታሁ

በልም ጎይ አስጣጥብ አሁለፌ በል - በለክ አስበክ አሁን ቃል ግባ

ለፈበል ለፈበል ለፈበል ላጊርደ - ቃል ግባ ቃል ግባ ለሀገርህ

አኡናም ጉይ ተጊና ተመካን ዘሚደ - ሰርተህ እለፍ ወንድምክ እንዳይቸገር

ቀደም ሲል የተመለከትናቸው ስንኞች ለፊ የሚለው ቃል እንዴት ለስራ ማነሳሻነት እንደሚውል ያሳየናል፡፡ እኔ የእከሌ ዘርነኝ እያልክ ስርቶ በከበረ ሰው ስም ከምትኮራ ዛሬ ያንተ ጊዜ ነውና ሳያልፍብክ፣ ጉልበትህ ሳይደክም እወቅበት ነገሌላ ቀን ነው ምን እንደሚመጣ አይታውቅም፡፡ ለልጆቼ ምን አስቀምጨላቸዋለው ብለክ አስብ፡፡ ተፅፅተክም ለመስራት ቃል ግባ፡፡ ዛሬ ቃል ገብተክ ከሰራህ ያንተ ታናናሽ የሆኑ እህት ወንድሞችህ አይቸገሩም፣ ለሁሉም መከታ ትሆናለህ፡፡ ቤትህ ሞልቶ እንድታይ ጠንክረክ ለመስራት ዛሬ ቃል ግባ በማለት ስለ ነገ እያሰበ ብርቱና ጠንካራ እንዲሆን የሚገፋፋና ለስራ በሞራል እንዲነሱ የሚያደርግ ቃል ነው፡፡

### 3.2.5. እዲሽ ባላገር ነው

**እዲሽ ባላገር ነው**፡- እኔ ባላገር ነኝ የሚለው ዘፈን ግጥም በርዕስነት የተመረጠውን የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ የገጠሩን አኗኗር ስልት፣ የገጠሩን ማህበረሰብ የልጅ አስተዳደግ ምን እንደሚመስል እና ሌሎችም ጉዳዬች የተዳሰሰበት ነው፡፡ይህ ዜማ ባላገር የሚለውን ስያሜ እወደዋለው የማንነቴ መገለጫ ነው፡፡ ባላገር ተብዬ ካልተጠራው ምንም ስም ሊወጣልኝ አይችልም፡፡ነገር ግን የማያውቅ ሰው ባላገር የሚለውን ስያሜ በሌላ ከተረጎመው እሱ የሚፈልገውን ይጠይቀኝ እኔም የምጠይቀው ብዙ ጉዳይ አለኝ የሚል አሳብ የያዘ ዝፈን ነው፡፡

የዘፈኑ ግጥም መልህክት ምን እንደሚመስል ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ኽዲሽ ባለገር ነው ባገረ - እኔ ባገሬ ውስጥ ባላገር ነኝ

ሂነሂ ዝምነው ዘንድረ - ዘንድሮም ይህው አለውኝ

የቶለድኩ ባገር በሰት እስት ምድር - የተወለድኩት እንሰት ያለነት ዘገርውስጥ ነው

አምባቸውም ላኩም በገርገቲ ስር - ምድጃ ስር ተንፈቅቃ ነው የሰኩት

ሞሳውም ዘለልኩም በፊዩ ጓጌት - በጊቢዬ ውስጥ እንደ እንቦሳ ጥጃ ዘልዬ ነው ያደኩት

ጥጋገ አበለላሁም ለቀምኩም ክበታ - ጥጆችን አገጄ ኩበት ለቅሜያለው

የቡሬ የበላጭ የጋሬዲ ኽፋተ - ዝንጉርጉር ጠሆኑት ጠላሞኤን ወተት

ስጤሁምንየላቅኩ በፊዩገየተ - ጠጥቼ ነው ያደኩት በደናው ቀዬ (ሰፍሬ)

ከላይ በተጠቀሱት ስንኞች ባላገርን እንዲህ በማለት አስተዳደጉን እና ውበቱን በሚያያዝ ይገልፅዋል፡፡ እኔ በሀገሬ ውስጥ ባላገር እየተባልኩ ነው የምጠራው፡፡ በፊትም አሁንም መጠሪያዬ ባላገር የሚለው ስሜ ነው፡፡ የተወለድኩት እንሰት በሞላበት፣ አየሩ በሚስማማና ነፋሻ በሆነ ቀዬ ነው፡፡ ለቤታችን ብርሃን እና ሙቀት እንዲሰጥ እንጨት በሚነድበት ምድጃ (ገርገት) ዙሪያ ተንፏቅቄ ነው ልጅነቴን ያሳለፍኩት ካደኩም በኋላ በለምለም ሳር በተሞላው ቀዬ እንደ ጥጃ ቦርቄ እንደማኝኛውም የብሔረሰቡ ተወላጅ ከብቶች አግጄ፣ ለቤተሰቦቼ ኩበት ለቅሜ የምወዳቸውን ላሞች ወተት ጠጥቼ ደስተኛ እና ጠንካራ ሆኜ ነው ያደኩት፡፡ ይህን ደስታ ማግኘት የቻልኩት የተፈጥሮ ገፀታውን ባላወጣው ባላገር ተወልጄ በማደጌ ነው፡፡ በማለት የተወለደበት ቀዬ ውብ ገፀታ በመግለፀ ያደንቃል፡፡

በመቀጠልም ባላገር ነኝ ብዬ ብነግረው በባላገርነቴ ተዘባበተብኝ በማለት በሚቀጥሉት ስኛኞች እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፡፡

ኽወድዲ ሀረር ዘ ኩሊው በሸለ - ይሄ ሁሉ የሰጠኝን ሀገር ብነግረው

ባላገርን ባሌው አገር አይሽለ - ባላገር ነህ አለኝ ስለባላገርነት የሚያውቅ

ኽዲሽ ባላገር ነው ጊንዶ ቀንበር ዩዘ- እኔስ ባላገር ነኝ ቀንበርና ሞፈር የሚይዝ

ቁናማይ ተጊኖ የዲ ኽጅ ታይቀምሱ- አንደቀን አይታደርም የኔን እጀ ሳይቀምሱ

ዝባበርክም ሆድኬ እንደኽ ችላ በሌ - ደጋግመክ ነገርከኝ እባክህን ተወኝ

አታሊቅ ልበደ ኧሸኮ ታሻሌ ዘማሌ - እራስክን አታኩራራ ጠይቀኝ እጠይቅካለው

ይህን ሁሉ የሰጠኝን የተወለድኩበትን ቀዬ ባላገር ነው ብዬ ብነግረው ተዘባበተብኝ፡፡ ስለ ባላገር ጥቅም አለማወቁ እንጂ ሞፈር ቀንበር ይዤ ለሀገር ለወገኔ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳልል አርሼ ምርት የምሰጠው እኔ ባላገር ገበሬ እንደሆንኩ ባለማወቁ

ናቀኝ ነገር ግን ከተሜው የኔን እጅ ሳይቀምስ መዋል ማደር አይችልም፡፡ ደጋግመክ ደጋግመክ ባላገር መሆኔን ነገርከኝ፡፡ የተወለድኩበት እና ያገኩበትን ባላገር ገፀታ ስለምወደው በኩራት ገለፅኩልህ፡፡ አንተን ደግሞ ልጠይቅህ መልስልኝ የከተማው ኑሮ የተመሰረተው በማን ይመስልሀል? ይህን ባታውቅ ነው እንጂ ደጋግመክ ባላገር የሚለውን መጠሪያዬን ካለ መሰልጠን ጋር አያይዘክ ባልተዘባበትክብኝ ነበር፡፡ የሚል መልህክት ነው የሚያስተላልፈው፡፡

በመቀጠልም ባላገር ሁሉ ነገር በእጁ በደጁ በመሆኑ መጠሪያው እንደሚወደው እንዲህ በማለት ይገልፃል፡፡

ኸዲሽ ግዘዳይ ነው ዘንድር - እኔስ እርኛ ነኝ ዘንድሮ

ኩልቀይ ባለቦ ባገር - ሁሉ በመላበት ባላገር

በገንቦዲ ቅሸው በጌላለ አተር - ከታች በኩል አተር ከበላይ ባቄላ

በጌታተ ስር ባረዶ ምሽት - ለም በሆነው መሬት ምስር አለኝ

አመት ላመት አዲ ሙለን ስዋትዲ - አመቱን ሙሉ እጥዳለው ሙሉ ነው ጎተራዬ

አምቦል ጊሽ ዩቤው ዩደንቁ ኋረዲ - ጎመን እና ጌሾ የሚሰጠኝ ጓሮዬ ያምራል

ውራውሬ ዩስብሩም ጎይ ይስጉ በበርዲ - ከግንድ ጫፍ ተሰባብሮ መግቢያ ቤቴ ላይ ይደግልኝ

ሰም ያውጠሊ ለዲ ዩጥረኝ ባገርዲ - ስም ይውጣልኝ ለኔ ልጠራ ባገሬ

ዘንድሮም ሁሉ ነገር በሞላበት ባላገር እረኛም ገበሬም ነኝ፡፡ ከቤቴ በላይ ባቄላ ከቤቴ በታች አተር በለመለመው ጓሮዬ ምስር፣ ገብስ፣ እና ጌሾ የሞላኝ የዘራውትን አመት ላመት አጭጄ ጎተራዬን የምሞላ ባላገር ነኝ፡፡ ይህ ተግባሬ ደግሞ በአገሬው ጀግና ተብዬ በብሔረሰቡ ዘንድ ወንድ ሙሽራ ሲያገባ የሚሰጠው ቅጠል ተሰብሮ በቤቴ መግቢያ ላይ ይደረግልኛል፡፡ በአገሬ ይህ ያህል ክብር ይሰጠኛል፡፡ ምንም ይሁን ምን እድገቴን፣ ማንነቴን ኑሮዬን በሚያስታውሰኝና በምኮራበት ስሜ ባላገር እየተባልኩ ልጠራ ከሱ የተሻለ ምንም ሊወልኝ አይችልም የሚል አሳብ የሚገልፅ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ እኛ ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ወቅት የምዕራባውያንን ባህል በመከተል የራሳችንን ማንነት እያጣን ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስተባት ለሚቀጥለው ትውልድ መጥፋት ምክንያት እንዳንሆን ከአሁኑ የሀገር ፍቅርን፣ በማንነት

መኩራትን፣ የራስ የሆነን ነገር መውደድና ማድነቅን ልናስተምራቸው ይገባል የሚል መልእክትም ያስተላልፋል፡፡

## 3.2.6. ምኔቦ

**ምኔቦ፡-** የሚለው ቃል በርታ ማለት ሲሆን ይህን ስነ-ቃል የሚጠቀሙበት ለስራ ማበረታቻነት ነው፡፡ የዚህ ዘፈን ግጥም የሚያመለክተው በርዕስነት የተመረጠው የክስታኔ ጉራጌ ብሔረሰብ የሚተዳደረው በግብርና ሲሆን አንድ ገበሬ መስራት እየቻለ በስንፍናው ምክንያት የሚያጋጥመው ችግር እስከ ምን ድረስ እንደሚሄድ የሚያሳይ ነው፡፡

የስነው ኪት ኸስት ነበሬ በጓራ - ያቅሜን ያህል ጋሮ ሁለት እንሰት ነበረኝ
ማኙም ጎይ ታዬቡ ነፈጉም ዬባራ - ተንቆ ሳይሰጠው ቀርቶ እበት (ማዳበሪያ)
ተማኝ ታንነጭ ታኸርንን በላተ - ንቂው አረሙን ሳልነቅልለት
እነዚጭ ነገ ሲስተ ተብል ሳምንተ - ዛሬ ነገ እያልኩኝ ሳምንት ሆነኝ እና
እኘውም አረጠቢም ምባም ግፋተ -ሳልንከባከበው ንቂው መሃል ለመሀል ተቆርጦ ወደቀ

እነዚህ ስንኞች አንድ ገበሬ ተፈጥሮ ሳታዳላ የሰጠችውን ሃብት መጠቀም ተስኖት እንዴት እንዳጣው ይገልጻል፡፡ ይህ ገበሬ የጉራጌ ብሔረሰብ የተለያዩ የምግብ አይነቶችን እያዘጋጀ ለእለት ተዕለት ኑሮው የሚጠቀምበትን እና በማንኛውም የአየር ፀባይ ሊበቅል የሚችለውን እንሰት እንኳን ገንዘብ በማያወጣበት እና ከቤቱ በሚያገኘው የከብቶች ተዋጽኦ (እበት) መንከባከብ አቅቶት በስንፍናው ምክንያት መሀል ለመሀል ተቆርጦ እንደወደቀበት ይገልጻል፡፡

ስንኞቹ የሚያስተላልፉት ሌላው መልእክት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በቁም መረዳዳት እየቻልን አንዳችን ለአንዳችን ባለመተዛዘናችን፣ እራስ ወዳድ በመሆናችን እና የሌሎች ችግር ግድ ስለማይሰጠን በቀላል እርዳታ መትረፍ የሚችል ወገናችንን በቸልተኝነታችን ምክንያት ምን ያህሉን እያጣን እንደሆነ የሚያመላክቱም ነው፡፡

በመቀጠልም በስንፍናው ምክንያት የእለት ምግቡን ያጣው ገበሬ እስኪ ሰዎች ምከሩኝ ምን ይሻለኛል በማለት ችግሩ ምን ያህል እንደጸናበት ይገልጻል፡፡

ኸእክ ምንን ስቦች አውድሙኝ - ሰዎች ምን ይሻላል ንገሩኝ
ምን ዬኩን ዋራተ በሰተ - ምን ላድርግ የስራ ጊዜውን ዘነጋሁት
ኸስት ያርጥቢየን ሳርዲ - ሳሩ አድጎ እንሰቱን ሊቆርጥብኝ ነው

ጉንሰ ይኮላዬየን በጌዲ - ምግብ ሊያሳጣኝ ነው በቤቴ
ታኾን ታኾን ዬዜው ጊንዝዲ - እያሁት ችግር ያዘኝ
ፊትል ቀበጥበት ኪሲዲ - ክር እንኳን ታጣበት ከኪሴ

ገበሬው ወቅቱን ጠብቆ ባለማረሱ ጎተራው ባዶ መሆኑን፣ ጓዳውን ችግር እንደጎበኘው እና መስራት እየቻለ ባለመስራቱ ችግር እግርና እጁን እንዳሳሰረው ይገልጻል፡፡ ሌላው ቢቀር አርሼ አምርቼ ከቤቴ አልፎ ለገበያ ያወጣሁት ምርት ባለመኖሩ በኪሴ ቤሳ ቤስቲን አይገኝም፡፡ ይህ ደግሞ ድንገት ብሞት እንኳን ለመገነዣ የሚሆን ክር መግዣ በኪሴ ባለመኖሩ ሁሌም የስንፍ ምሳሌ ሆኜ ሲተረክብኝ ይኖራል በማለት የሰራው ስራ ምን ያህል አሳፋሪ እንደሆነ በዚህ መልኩ ይገልጻል፡፡

በሚቀጥሉት ስንኞች በስንፍናው ምክንያት ብዙ የተማረው ገበሬ ከሱ ባሻገር ሌሎቹ ችግሩ እንዳይገጥማቸው እንዲህ በማለት ለስራ እንዲነሳሱ ያበረታታል፡፡

ኸዡ በል ተበይነትን ዎውድድ ዋዛላ - ከልጅነት ነው ስራን መውደድ
ንባሮት ቲኮን ዬሰብኒ ዊላ - ኑሮ ላይሆን የሰውን መመኘት
በጆ ያሊዙ ቀይ ዎዥ ምን ዬዶፋው - በእጅ ያልያዙትን ነገር ማየት ምን ያደርጋል
ሙጫ እግዜ ዋበል እነዝ ያለፊው - ዝም ብሎ እግዜር እግዜር ማለት ልፋት ነው

ከላይ የተገለፁት ስንኞች ጠቅለል ያለ ሐሳብ የያዙ ናቸው፡፡ ይህም ከልጅነታችን ስራን መውደድ አለብን፡፡ የገንዘብን ጥቅም ለፍተን ደክመን ስናገኘው ይገባናል፡፡ የሰውን ብቻ ማድነቅ እና መመኘት ምንም ጥቅም የለውም፡፡ ሰው የደረሰበት ለመድረስ ዛሬ ስንፍናህን ትተህ ለስራ በብርታት ተነሳ፡፡ አሁን ሰርተክ የምታስቀምጠው የላብክ ውጤት ጉልበትክ በደከምክበት ወቅት ቁጭ ብለክ ትበላዋለክ፡፡ ይህ ሳይሆን ግን እግዜር እግዜር እያሉ ወደ ሰማይ በማንጋጠጥ የሚመጣ ለውጥ የለም፡፡ እነደ እግዜር ትዕዛዝም "ጥረክ ግረክ ብላ" የሚለውን ቃል በመፈፀም እራስክን ቤተሰብክን እንዲሁም ሀገርክን ስትል ስንፍናህን አስወግደክ ጠንክረክ መስራት አለብክ የሚል መልዕክት ነው የሚያስተላልፈው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት የፀጋዬ ስሜ ባህላዊ የዘፈን ግጥሞች በሁለት መንገድ በመክፈል ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በመጀመሪያ ስር ጋብቻን ብቻ በማስመልከት የተዜሙትን በመከፋፈል ትንተና ተደርጓል፡፡ ሁለተኛዉ ላይ ከጋብቻ ዉጪ ያሉ ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያነሱትን ዘፈኖች እንደሚያነሱት አሳብ በመከፋፈል ለማየት ተሞክሮዋል፡፡ በዚህ ክፍል ዉስጥ የተካተቱት ብሔረሰቡ የተለያዩ ሁኔታዎችን ለመግለፅ የሚጠቀምባቸዉን ስነ-ቃሎች የያዙ ዘፈኖች ናቸዉ፡፡ አርቲስቱ በአጠቃላይ 35 የሚሆኑ ዘፈኖችን የተጫወተ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 10 የሚሆኑት በሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች ተዜሙ በመሆናቸዉ እና የተቀሩት ደግሞ ፍቅርን ርዕስ አድርገዉ የተዜሙ ስለሆኑ በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ አርቲስቱ ከተጫወታቸዉ 35 ዘፈኖች ውስጥ የብሔረሰቡን ባህል በደንብ ያሳያሉ፣ ይገልፃሉ የተባሉት 10 ግጥሞች ብቻ በመምረጥ ትንተናዉ ተደርጓል፡፡

አሁን በተደረገዉ ጥናት ዉስጥ የብሔረሰቡን ባህሎች በዘፈኖቹ ግጥም አማካኝነት በጥቂቱ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን ብሔረሰቡ ብዙ ሊጠኑ የሚችሉ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ባህሎች ስላሉት እንዚህ በስፋት መጠናት እንደሚችሉና መጠናት እንዳለባቸው ሳልጠቁም አላልፍም፡፡

# ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

- The derivation of the term lyric from “lyre” a musical instrument relates the genre to song, suggesting brevity. A strongly musical component a significant presence of emotion and a direct involvement of the singer or pet page 175

- Alyric /from the Greek and yricos/ was originally a song written for musical accompaniment by a lyric. The term now refers to poems that although not necessarily intended to be song are  melodies in meter and tythm page 476

- Lyric is apoem written for music page 26.

# ዋቢ ጽሑፎች


**ሊሻን ተፈራ** “የአስናቀች ወርቁ የፍቅር ዘፈኖች ግጥም ቅርፅና ይዘት ግምገማ” ዲማፅ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ክፍለ ትምህርት የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974።

**ሰላማዊት ይልማ** “1987 — 1990 ዓ.ም በካሴት ታትመዉ ለገበያ የዋሉ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ቅርፅና ይዘት ትንተና” ዲማፅ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ትምህርት የቀረበ፣ ኢስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 1991።

**ብርሃኑ ገበየሁ** የአማርኛ ስነ ግጥም፣ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 1999 ።

**ኃይሉ ገ/ዮሐንስ** (ገሞራዉ) በረከት መርገም፣ አዲስ አበባ 1966።

**አለማየሁ ጌታቸዉ** “አርቲስት አለማየሁ እሸቴና ስራዎቹ” ዲማፅ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1993።

**ዘሪሁን አስፋዉ** የስነፅሑፍ መሰረታውያን አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት 1998።

**ድንበሩ አለሙ እና ሌሎች** ጎንት፣ የጉራጌ ብሔረሰብ ታሪክ፣ ወልቂጤ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት 1987 ዓ.ም።

**ጎራዉ ሳልለዉ** “የአያሌዉ መስፍን ዘፈኖች የይዘት ትንተናና የሴተኛ አዳሪዎች አተያይ” ዲማፅ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሑፍ ክፍለ ትምህርት የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1984።

Academic American Encyclopedia

Cdar lewis The lyric impuls. London, Ehatto and windus L.T.D 1965.

Ruth miller Robert a greenbery. Poetry An introduction, Hong kong. Macmician education L.T.D, 1981.

# አባሪ

## እንሾሽላ

ትልበስ ነጠላሂ እንጮት  ዬጨጭላ

ዘመድ ዬሰብስብም ኸሹ ኸፋት ዬብላ

አብምጎይ ጉታኃን ዮቶና በማስ

እልል ዬበልላ በግፍት ዬዶርሶ

እንሾሽላ
እንሾሽላ

| | |
|---|---|
| እንሾሽላ ያግድልኮ ሳይ | አቢቅጦ በላ |
| የኑረና አምባሬ ጊሚሴ ቀሽት | እሚት ቅጦ በለ |
| የዳሙ ዋገራም ሜድኮ ዘመቴ | ዘሚ ኢኔው በለ |
| የዋጮ አሪትጌ አማወቴ ገሬኖ | ኸቲት ኢኔው በለ |
| የአይገዶ ኸሽገድየ ከንዝ ጎተራ | አንሳቢ ኢኔው በለ |
| የእንደቡየ የአይመለል ዝጋን አንገትጌ | ኸማየ ኢኔው በለ |
| የአደሌ ድግላ የአዲስ አበባ | ኸታቦየ ኢኔው በለ |
| ኮልምዬደ በለ | እንዶቶ ኢኔው በለ |
| | የክስቶነው በለ |

አዎኝሽ አዎኝሽ ዬዥልችን ጂላልደሽ

ዬውጣ እጮት ዬጨጨየ ሻማ ስከር ያክላልቱየ

ትቶና እት ዬድምቅባመ አቢሂም ዮዝ ዮቶናመ

ዘመድ አዝማድ ዮሰከሰከም እንሾበላ ዮበል ኵልም

ዮዥ ገረድ በግፍተ አቢእሚት ያትፈሳተ

አትም ምካት ታይሰለባ በፉት በቅበ ዮላቀተ

አሆኝ እንሾሽላነ አሆኝ እንሾሽላነ አሆኝ እሾሽላነ

ጥወርሙ ገዳዋንነ

አሆኚ አንሾሽላነ አሆኝ እሾሽላነ

ትድመቅቦ ቀኒ ዮኪያትነ

አዎኝሽ የደኸየ ብጤ ዘመድ በጌደየ
መጠሙመ በስተተ ዮደርሰሙን ኸገት ኸገተ
ሻማ ስከር ሺለሙመ አቢ እሚት ቶናመሙ

እንሾሽላ ይበልሙነ እግዜር ነዘ ያስለነ

ተጎሽም ጎሽ ገምያነኸ አቢ አሚት ያትፈሳኽ

ተንሳም ድረስ በገዳደ አሁ ታለ ጎይ ጊንዥደ

እንሾሽላ እንሾሽላ

ዮበልላ

እንሾሽላ እንሾሽላ

ዮበልላ ዮበልለ

## ዬዋሬ

ዬዎሬ ዬዎሬና ገረዲ አችምና

ዬዎሬ ዬዎሬና ገረዲ አዝምና

ዬዎሬ ዬበሷ ገረድ ደመቀባም

በንድረ ይሰበቱ ዬላቱይ ኮነላም

ዬዎሬ ዬባሷ አገርከተት ዬሰማ

አቢ እሚት ያትፈሳት ኪያትና መልካማ

ዬዎሬ ዬበሷ ሰምኪ ጠበቀትም

ዬበሷ ቀይ ስማትም ሰቢም አትፈሳትም

ዬማና በባሉ ጌሂ በሸሸሉ

ምድር ብስታኔ ኪያትና ዬበሉ

አቢሂም ዝምነ ሰዋተው ሙለነ

እሚትኪም ልባም የገረድ ቀንጡና

ሜትዬም በሻሉ ሰባት ጌዋነ

ቲወዱም ቲያበቀለ ያገሪን ቸባነ

ኢሚትደሽ ኧቲተ የደሽ እንደትየ

ከርሶ ትዳብሲ ትማሺ ኩትያ

የደኮደሽ ዘማች የደሽሽ ኧማየ

ቢኮንሙልች ብዠገረ ቢቲዋየ

ገረ ኢነንሹ አንሳቢ ኧታቡየ

እንኳም ለጉባደሽ ለገረነም ዋጋየ

ዬዎሬ ንበልን ነዚ ነዘሚኛ

ዬሽኒ አገኘም ዋደድነለም እኛ

አለንጋዋን ቢዘም በፈረሰ በቶና
ዬስለቦም ዬለ የፈረዝየን አና
ዬዎሬ ንበልን ንጡር ባናትኛ
አቲዝነም ማረግ ማለቂ ዘሚኛ
ልበስም ጎይ ነጨ ቶናም በነጨ
ትሰላም ትመጣው ዬለበኮ አንብላጨ
አርምድም ጎይ ዬዝም ቶናቦ በዳማ
ኢሚርቁም ዬብኮ ቅመጩ መልካማ
አሚርቁም ዬብኮ ቅሙጩ መልካማ
ቶናም ጎይ ዬዎሬ ዬበልኮ
ተጠምጠምም ውጣ ጉርዚም የመረከ
ሂሚደ አዮደሌ የደኸ ኸማየን
ምካት የሺልቱ ጥፎ ናታዥየን
ያቢደ ኸታቸ የደኸ ኸታቡየ
ቢመጣም ነግዳ ቲስጥም ትከየ
ጎሼ ኢነንሆ  አንሰቢ አንዶትየ
በትር ዮኮንሙኮ የምካቲ ማየ

## ልሙ የኩንኮ

ዬበልለ ለኳ ዬበልለ ለኳ ዬበልለ ለኳ ላቢ
ዬድብልቦም ያገባ
ልሙ ዮሁንከ በልሙ
አውነሙለ ካባ ዋይ ጋቢ
ዬበልላ ላኪያ ዬበልላ ላኪያ ለሚት
ትድበልቦም ታገባ
ልሙ ዬሁንሽ በልሟ
ትልበስ ትድመቅ ትንግሊሊጥ
በጋመደ ታፈር በጠወረም ጊንዳ
ባባለትም ምድር ባርሰም በዘራ ታያዋና ኸደጉት ኸዳ
ሁሎ ተጥቤና ቁንጣ እንገለደ

ቢሰበ ምዛለ ይዘኝጎይ አልደል ምምሽው ብሩም ባለሊየን

ባደደም በቢት ዬውዘተው ባዥ

ታይተክምም ታይሰጨ ዘትንጎይ ይገራ እለን ቡዥ ቡዥ

ቢኪደም ባገባ ሰዋተው በሞላ

ሂፍተው ይዝባብርም ሴላ ቀይ ዮሰቡ የኗኒ አትሙ ቲሞላ

በሺከተም ንባር ግበር በነገደ

ተዚተዛ ቲብል ጌዋን ነዋትፈሳ ሆኝ ብሩም ባልዎደደ

**አቤሽ** ባትመረም ባየኃን ፈያ በሰለተ

ኸረ የኗሆም ማኒ አይከፋሉ ኸገተ

ዬበልለ ለኗ ያሸንት ዬዋሬ

ባለፈም በሽሌ ባለቀም ባትመሬ

ሄቦ ሄቦ ዬበሉ የነሶም ዬድርሱ

ባለም ዎንብር ፊያን ኸድሜ ያብከ በልሙ

በሞተም ኸገትን ፊየኃን ዝገድሙ

በከርስ ትናለ ትለግድት  በጂኪ

ቀነ ትቆጥሪ ብሩሙ ትዳጊ በምን ታዥ ድረስ ቢንኪ

ባኒጠስን ባዝንት በታዥ ያዥናትን

ምስደብ ታበዘይ ትበድርም ትቂጢ ገና ታይሞት ትሞትለትን

ሌማት ሙሉ ከሽት ብተብ ብታበላ

ቲወስላ ይገሮ ታይረብን ትረቢ ትብሊ ኸዲ አፈር ሙለ ነብላ

ምዘለም በፈካ ዬትመርይ ባለፈ

ፈያ ይኖ ትትብል ኩልጎይ ጥበትን አለመትኪም ስርም ቲያርፍ

**አሚትሽ** ብትጦር ብታላቅ ታይከሸሸ ጊንዧሂ

ብታጥቦ ብታለብስ እሚት ለባይሂ

ዬበልላ ላኪያ ያሽናት ዬዎሬ

ልሙ ዬኩንሽ በልሟ ባሙት አለምብሬ

ዬምን ዬሞተት ማይ ይዘሉ ያቦሱ

አሁ ኢቲ ኢቲ ዬበሏ የነሶም ዬደርሱ

ምን ዬጋይልሽ በልሟ ትብሰቅ ትትበላለቅ

ልፋትኪ ጡር ያግኝ አሁም አሁም ትድመቅ

## ወሴ ባሳ

ዚ ባሉት ምንነ

ዚባሉ ዛባሉት ምንነ

ነባሉ እንዝን  ባለቡ

ባሉም ባልትሰራ ብሩም ቦራ ባለለቡ

ሸንጎ ተምን ዋለ በባሉ

ኸከሌ ገደሉት ኸከሌ አገዱት

ምድረ አከፈሉት

አገርሽ ምን ባለ በምን ዋለ

አትም አልዘበረ ከሸትም አልበላ

ሂኖ እናደረ

ኧረታው እንዝን ኬረቃይ ስማ

መጥረም ፊያው አጥመማ

ባልኮነ ፈያሆም ዬድፍንን

ተፈዩ ጥፎዩ ባሽንን

ባሉትን ዚ ተዛ ቂኖትን

በጀረ ምድረ አረሱትን

በሰሙ በእንዝን ባጥመሞ

ያርጡትን ቀስላ በገንዘሞ

ወሴ ወሴ ወሴ ወሌ ባሳ በልን

ተፈዬ አትጣድን ጥፎዩ ቃይ ጥላንን

አያገፑ ቀይ ባገፑ ወሩ በስለቱ

እንዝን ኬር ባልሰማ ንባር ያስለትቱ

ምኒሆን ትናለ ባሉት ባልትረሳ

ወሴ ባሳ ንበል አሁም ወሴ ባሳ

ኸከሌ ሂቲዋለ ባበሉ

ጌዋን ቦረሰንም በቡላልጌ ቶናም

ምድር አጢላንም

ስቢ ኽኽክ ምን ባለ በሻለ

ያቢ ምድር ከሎት ቢቺፋ ወደረ ሺከቱም አገዱት

ኽረታው እንዝን ኬር ቃይ ስማ

ተጥፎ ፊያው አጥመማ

ጥላቦ ባሉት አታሩሽንን

ዝባብርም ወሴ ባሳ በልን

ኢን ብርቱን ፊያ ጥፎ ያዥ

ልብ ገዋን በባሉት ይብረዡ

ባገሪ ባሉት ባልትረሳ

ዬዝባብሩም ዬበሉ ወሴ ባሳ

ቀኒ ባልመጠረም ተምሽተው ባልቶና

ጉባኃን ያጥለስም የሰብ ጌ ባቀና

ምሽተም ጌ በሳተት ሚዲ በጫመና

ዚ ባሉት ዛ ባሉት አመል በኮነና

አያዥ ቀይ ባዡ አይኮን ቃይ በኮነ

ዬስባከሩም ኅይ ቦሻ ባሉት ታይፊጀነ

ዚባዥ ታይቅስ ዬጠሩም በሳንሳ

ዬቁሙም በገደል ዬበሉ ወሴ ባሳ

## <u>ኬርዬኽ፟ን</u>

ዬሁን ዬሁን ኬር ዬኽ፟ ን ኬር

ለችባኒም »

ለቅበቲም »

ለገየቲም »

ለኀርደናም »

ላቀተኚም »

ለከተቲም »

ለኢትዮጵያኛም »

ያዋሩዬ ምን ዬኮን ዬስሞዬዎ ምን ዬሁን

ዬሚርቂም እግዜር ዬኩን ዬትሚረቂም ስብ ዬሁን

አገር ከተት በሙለ ሰኘት ዬምብር በምድረ

ስኛት ባለ በምድር ዬደረ አደል ምን ቲተረ

ዚ ያኸዮ ብልቃት የትፈሲ በሙለ

ቢለብሱም ቢደንቁም አገር ስኛት ባለን

ፊያ ባወረሩም  ያጥመማ ባለ

ቲፋትየን አልደበል ተፎለየን ዬለ

ዬኩን የሁን ላለመ

በምድር ላሲ ኩልመ

ሰኞት ባለ ባለመ

ምካት ቲነብር ስርመ

ኧዲሽ ባርዲ አትዬኖ ብላተ

በሙሊ አንገዶ ዬሲር ሞፈን ባለ

መሴር ዬዎቀለም ጠማኻን ያግዱተ

በኻም በልኮነለ ፊያ ዬዎቅጡተ

ኳም ዬሽክትትን ኬርም ዬኮንለተ

ዝትሆምትን ብልሃተ

ዬኳትንቃይ ዬሺልተ

ቲሾሉ ዬሽሉት በስተተ

በሳትበሽዬሽሉተ / ዬሰሉተ/

| | |
|---|---|
| ለክስታኔ | ለአቅኚም |
| ለዶቦዬም | ለጉርዛዘም |
| ለምሁሪም | ለአርዴዬም |
| ለቸሃሰብ | ኩልኩለው |
| ለኧዛስብ | ለምደርኛ |
| ለስባትጌ | ለከተቲም |
| ለወለኔ | ለኢትዮጵያኛ |

ስመም ዬኛ ስበች ከተቲ በሙለ

በቱጋገትነ ፊያ ዬሰላብነም ዬለ

ኧብረ በውዘየነ ቁናይ ባሰኘነ

ባላብነ እንዝንኛ ዚባሉት በልበልነ
ንባርም ንነበሩ አትም ተደበነ

**ዬሻልቢ**

እሆተኳ አልመን ጎሽ ዬለ
አዬ ተኳ አልማን ጎሽ ዬለ
ብሩም  ባኄጌ ጎሽነ
ሰርም ተኳ አልማን ስብዬላ

ዬሽልቢ ዬሻለ (4)

በዋባም ጎይ ድብር በገደለ አንበሳ
ባጆም ጎይ ዘሚኃን በዛረገ ኽሬሳ
በሰበረ ውድማ በከረ ረሃኝ
ቅናን በሳጠም ጎይ የምሽት ባልኝ
ኽጣይ ባገድቦ በገንቦ በፈታ
በተኃን በስጦም ጀራረ በነታ
ያረደኒ ሞፈን በሳይስት በፈጀ
ሂፍታው ባንብራጣ ኢነው ኽስኮከም ባጀ
ዚትኖይ ገሚያነት የጎሽ ዋልድ ያኽቦ
አሹ በርታ አቦዶ አቦጉሽ ይብልቦ
ግላጀ ምግልድ ኖይ ምሽት ምስ ያትቢለ
ቀሚስ ተወንደቢት ለምድ ጉግረ ታለ

ለዷ ያሊዬ ዘ ዬሻለን የጎሽ ዋልድ ያኽቦ
ለገር ለሰብ ሂስብ ፈያ አይቀብጥቦ

ምካት የሺልትም በምድር ያለድረስ
በሞትም ይዘግዱ ምዘላኃን ታደሰ

| | | |
|---|---|---|
| ዬሽለ | ዬሽልቢ | ዬሻላ |
| ባልሽለ | ባልሽለም | ዬሻለ |
| በሽለ | ባሻለም | ዬሻለ |
| በሳተም | በሳተም | ዬሻለ |

ቅናን ተመሽማን ባንጥላፋ ኩታ

ያለም ተመስልን የሰብ ቀይ ባልነታ

በጫነምጎይ ፈረስ ሽንጎ ምልፍ ባመጣ

በትር በጠወረም ገበያ በምጣ

ባቋራም ጎይ የጉርዝ ኧዲ  ኧሸሉ በባለ

ተዲ ሌላ አቾ ዬቶለድ ባለ

ቀስላ ያከሸቦ ቁንጥል በገለደ

ገቻ ዛንጀረ ሆም ወድል በዋደደ

ዚትኖይ ጎሽነት ማጫ ዬሰበርለ

ቢነብርም ቢሞትም አቦ ጎሽ ይበልለ

ዘሆመው በሞተ ከንፈርይመጥለ

ለዲያሊዬ ዚኧደል ኧረ ይኖጎሽነት

ኧግር መመር ያለን ዬሎ የገንድነት

በቶናም ቢቆምም ስሽብ ግርግያለቦ

አምፋት በዝባበረ ፈያ አይቀብጥቦ

## ኧዲሽ ባሳገር ነው

ኧዲሽ ባሳገር ነው  ባገረ

ሂነሂ ዝምነው ዘንድረ

ዬቶለድኩ ባገር በሰት ኧስት ምድረ

አምባቸሁም ሳቅኩም በገርኹ ስር

ዋሳሁም ዘለልኩም በፈዬ ጋጌታ

ጥጋገ አበሳሁም ለቀምኩም እቦታ

የቡሬ የበለን የጋሬዲ ኧፈቱ

ሰቾሁምን የሳቅኩ በፈዬ ገየተ

ኧወድዲ አገር ዘኩለው ቢሸለ

ባሳገርን ባሌው አገር አይሺለ

ኧዲሽ ባሳነው ጊንደቀምበር ዬዞ

ቁናማይ ቲገኖ የዲ ኧጅታይቀምኩ

ዝባበርከም ሆድኬው እንደኧችላ በሌ

አታሊቅ ልበዶ ኧሽኮ ተሸሌ፣ ዘማሬ

ኽዲሽ ግዘደፋይ ነው ዘንደረ

ኵልቀይ ባለቦ ባገረ

በገንቦዲቅሾው በጌላለ አተር

ጌታተ ስር ባረዳ ምሽረ

አመት ለመት አዱመሉለን ስዋትዲ

አምከል ጊሽዬቢው ዬደንቁ ጓራንዲ

ውራውሬ ዬሰከሩም ኅይ ዬስኅ በበርዲ

ስም ያውጠለ ሊዲ ዬጥረኘ ባገርዲ

ኽለከሰም በጌዲአዝም ኅይ ወለተ

በቀብር ደንቻ ባለማ ኽስተ

ዎርጣባ ባወጣም ምድር ባባልተ

ባሳገር ባሌው ገየት በሽክተ

## ዎኔቦ

ስቦይ ስማ

ስቦይ ስማ ስማ ናልሰሚም አሰማ

የሰነው ኪት ኽስት ነበሬ በጓራ

ማኘምኅይ ታዬቡ ነፈጉም ዬባራ

በሞረ ባፍቻ ዬለማ ዋራተ

ተማኘን ታንነኝ ታኸ፞ንን በለተ

እንዝጥ ነገሲሰት ተብል ሳምንተ

አኘሁም አረጠቢው ምባም ግፍተ

በነሳ አጠፋንት ባኩም ባድድን

ኽዝምሳይ እልሜዳ ባሎ በሽንን

ኽኽክ ምንን ሰቦች አውድሙኘ

ምን ዬኩን ዋራተ በሳተ

ባደዘባ ተኘ ከሩሙ

አሁሽ ቢሞትም ተሰሳትተ

ኽስት ያርጥቢያን ሳርዲ

ኅስ ዬካለየየያን በጌዲ

ታኸርን ታኸርን ዬዜውጊንዝዲ
ፈትል ቀበጥቦ ኪሰዲ

**ኧኸየ በል** ዘሚም ዋኔቦ ኧቲት ዎኔቦ
አቢም ዎኔቦ እሚት ዎኔቦ
አርዴዎኔቦ ኩልምዎኔቦ
ንወዘይ ቁናየን ንትውጋገትቦ
አገር ይነኖ ኩልም በባልነ
በቁኒ ሌማት ባት በበላነ
ዚንሳ ዛኧዲግ በትቢቢልነ
ንሳኽ ቁናን ምኽት ቲዘነ
ዎኔቦ ዎኔቦ.....

ተካሰስ ጥፋቲ በጌዲን በዲያን
ሆንተሆን ዎኸር ሳትኩም በምነው ቁናየን
ቁናን የሞረና የጓሪ ኧስተ
በምነው ቅጥ ዬባራ ቤቡ በገተ
ምንም ኮም ቢያጊኖም ቢያድግለ ነዋሪ
ያፈቺ ቲገፑኀይ ባልጠማ ተጓሪ
እንዝጭ ዋራት ዋራት ባሉም ጢሮመ
አዝምን አልሳቱ ምጠሳይ ስመ

ከታቲኸ በታርሸ ሳቡኘት
ከታለቅ ገር ሰብ በዱለት
ከትምረች ፈያቃይ ለምለቅ
ዎትፈሳም ቦግቦ ሊምዳቅ
ተዝበበርም ሂፍተ ፎለደ ኧኸርንን
ሂቲነው ቢቲነው ተሸልን
ሁረ ግኮም ነበረም ቢብልከ
ስም ሁራ ንብሮት ቲኮንከ

**ኧኸየ በል** ተባይነትን ምውድድ ምዘላ
ንባሮት ቲኮን ዬስብኒ ምላ

በጅ ያሊዙ ቃይ ምኘ ምን ዬደፈው
ሙጫ እግዜር ምበል እነዝ ያለፈው
አታብዛ ምኘት ተንሳ ፈርሻታ
የፎለ ዩድቡ በስር ዋጋንታ
ሆረስ ባለብብ ኸረስ ፈጠነው
ኦን ግድ ባለብከ ንገድ ፈጠነው
ዎትማገር ባለበከ ታማገር ፈጠነው
ሂላሃ ድድቅ እጅን ፈጠነው
ወኔቦ ወኔቦ
ለፊበል

አዝ……….

ጎሽ አሁ ለፊ በል አሁ ለፌ
ነገ ሲስተ አትበል ሂኖሆ ሚኔው አትበል
በጌ ጊራ ያለ ንብሊ ምድረ
ምን ልግዴ ባሎ ልዩ ዘንድር
በወርድክ ባታተ በወጣኸ ገገራ
አትም ታመጣልከ ያቢደን አደራ
በጋ ውሽጣ ያለ የቆለጨ አርፍ
ዚ እማ ባልስገርከ ሆንከርም ቢደፍ
ለፌ በል ለፌ በል ለሀገርደ
አሁናም ጎይ ተገና ታመካን ባይደክ
ለፌበል ለፌበል ለፌበል ለጌደ ቲመካን አቢደ ታመካና
እሚዳ

አዝ……….

እዲ ባልባሎ ነው የብሎ ነው ዘር
አገርም ሞላዬም እገባው ዘንድር
ሆበሊ ገፋርም ታያታለፍ ሻልቦ
ነገ ሌላ ቀንን አሁ ተውጋገትቦ
ነባይ ባይዲ ምን አሆናሁለም

በልምዳይ አስጣጥብ አሁ ላፊ በል
ለፌበል ለፌበል ለፌበል ላገርዳ
አሁናም ኀይ ተገና ተመበካን ዘሚደ
አሁ ለፌበል አሁ ለፌበል
ለፌ ለፌ በል አሁ ለፌ በል
ኀሾ ለፌ በል
አዬ ለፌ በል
ኀኦ ለፌ በል

## <u>ያሁዪ ባሶ</u>

አዲ ያገበኝ ዛ ወራተ
ገና በጉል ማሳነተ
ሳምንት ቶናሁም ባገረ
መጣሂ አደኩም ሽገር
ዱዱቅ ዬበልቦ የመሶ
ተትላበኒ የሁዩ ባስ
ምኝት ቀበጥኪ ከሩመ
ተመሸም ቲዛኝ ስርመ
አቢና እሚትዲ ላክሙ ቢምባገር
ቦረስከነም ምጣ ታትዋል ታታድር
መሸማን ተከብረግግ ታንኘ አደርዱም
ፈጠነው አለፍኪ ዛኘት ተነሳሁም
ጌ ተዋግባደ ዬፍት ፋራኂን ሆድኙ
ታመድ ተሳር ንሳ ይጮኚ ባልሙኙ
ኽዲም ሳር ነሳሁም ገባሂ ተሄየን
ዬባልኝ ነስማ ነዛም በይ ነብልየን
ስብ ዬለዋ ይኽረ ዬሽሌ
አታውገንዶን እች ይብሌ
ያጥመመኝ ዬሽልሊ
ንባርዲ ታይሽልሊ

አግባ አግባ ባልኻመ

የማነሽል ነበድርም ነውርር ባዬውድኻም እዲ

ቢቲገኑ ነባል ምንን ነሻልነጉባዲ

ኸረ አገር ዬኸርሲ ምካተው አውደሲ

ቀሽትም ዬቶናሲ አመጎፍ ስላሲ

የፈረሲ ሃገር አጨበር ዬመስክር

ልለፍ ተጎጌ አዴሲ የጣፊአገር

ተመቂ ዬለምፋም ውድሲ

ወይናባ ቀጥናባ ነዘም ዬላክሲ

ኵልም ዬጠራራም በዚም ባዛም ያሲ

ዬቶና ጉይ ሽጎ ግርዝና ዬኸርለ

አዝ..........

ወይነሻ ዬምብሬ ታሻልኝ አትም

አሁትን ገዳደ ባሙኙ ፈጀነም

ፈጠነው ቁጥ ምበል ባይነብርበም ጥፎ

ተሽላ ትትሽሌ ቅብ አልማን እርግፍን

ንባር የሳደቀይ ተትፍም ምርቃት

ክነም ማጠርሙሊም ኸዲ ታንሽልላ

ምን ትውድድ ምን ትጥላ ኸዲ ታንሽልላ

እነዚ ሙጫ ዋንቅፍ የልብም ቲሞላ

ኪያ በዛ ዬጦ ሚሂ

ኸዲ በዚ ፈፋ አዠሂ

ናትመታይ ናይሆን ግቦ

ኢኽቦ ዬለ ያስፋፈቦ

ዬቡርሽት ወይ ኸዲ ነምጣ

ፎለ ዬድቡ ሰላም ምጣ

የማነሻል ነበድርም ናውርር ባዬውድኻም እዲ

ቢቲገኑ ነበል ምንን ነሻል ነጉባዲ